# የ ሰ ባ ቱ   ኪ ዳ ና ት

# አ ገ ር!

*ኢትዮጵያ፡ የአሥራ ሦስት ወራት ፀሓያማ ምድር ብቻ ሳትኾን፡ የሰባቱ ቅዱሳት ኪዳናት ቤተ መቅደስም ናት! ይህች አገር፡ ኢትዮጵያውያን ልጆቿን ይዛ፡ የኢትዮጵያዊነትን ጸጋ፡ ለዓለሙ ኹሉ በማበርከት፡ እስከዛሬ፡ ለሰባት ሺ አራት መቶ ዘጠና ስምንት ዓመታት፡ በነጻነት ለመኖር የበቃችበት፥ ወደፊትም፡ በዚሁ ህልውናዋ ጸንታ፡ ልትቀጥል የምትችልበት ምሥጢር እነሆ!*

\+ + +

# The Sanctuary of the Seven Covenants!

*Yes! The revelation of the mystery for the past, present and future survival of Ethiopia, not only as The Land of Thirteen Months of Sunshine, but also as the oldest free nation on Earth under God for a period of seven millenia, four centuries, nine decades and eight  years is outlined herein!*

------------------------

**አሳታሚ እና አከፋፋይ**
Publisher & Distributor
**ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት አገልግሎት።**
Ethiopia: The Kingdom of God Services
**መልእክት ሣጥን ቁጥር ፰፻፲፪**
**ስልክና ዕምነቅ ቁ. ፬-፲፮-፲፰-፹፭ እና ፫-፳-00-፹፭**
**አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ።**
P. O. Box 812
Tel. & Fax. 4-16-18-85 & 3-20-00-85
Addis Abeba, ETHIOPIA
**ወይም** or
P. O. Box 43262
Tel.: 301-587-8074 ~ Fax.: 301-587-1971
Washington, DC 20010-9262 USA.
Email: ekogyesus@aol.com
www.ethkogserv.org

**(የኢትዮጵያ ማኅተም)**

**(የሰባቱ ኪዳናት ምልክቶች)**

# <u>ሰባቱ</u>

# <u>ቅዱሳት ኪዳናት፡፡</u>

ረዥም ዕድሜ ባለውና ሕያው በኾነው፡ በኢትዮጵያ ትውፊት፡ ህልውናን አግኝተው፥ እውን ኾነውና በሰውነት ጎልተው የሚታዩ፥ በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ፡ በክብር ተመዝግበው የሚነበቡ፥ እግዚአብሔር አምላክ፡ ከፍጥረት መጀመሪያ አንሥቶ፡ ከሰው ልጆች ጋር የተካየዳቸው (በመሓላ የተዋዋላቸው)፡ ሰባት ኪዳናት ይገኛሉ፡፡ እነዚህ ኪዳናት፡ ከዚህ እንደሚከተለው፡ የተዘረዘሩት ናቸው፡-

፩ኛውና የመጀመሪያው፡ በአዳምና ሔዋን ሥርዓተ ጋብቻ ምልክትነት የሚታወቀው፡ "ኪዳነ አዳም"፥ (ዘፍጥ. ፪፥ ፳፩-፳፭፤ ማቴ. ፲፱፥ ፬-፮::)

፪ኛው፡ በቀስተ ደመና ምልክትነት የሚታወቀው፡ "ኪዳነ ኖኅ"፥ (ዘፍጥ. ፱፥ ፰-፲፯::)

፫ኛው፡ በኅብስትና ጽዋ ምልክትነት የሚታወቀው "ኪዳነ መልከ ጼዴቅ"፥ (ዘፍጥ. ፲፬፥ ፲፰-፳::)

፬ኛው፡ በግርዛት ምልክትነት የሚታወቀው፡ "ኪዳነ አብርሃም"፥ (ዘፍጥ. ፲፯፥ ፩-፲፬::)

፭ኛው፡ በጽላትና ታቦት ምልክትነት የሚታወቀው፡ "ኪዳነ ሙሴ"፥ (□ˆ■. ፭::)

፮ኛው፡ በዘውድ ምልክትነት የሚታወቀው፡ "ኪዳነ ዳዊት"፥ (፪ሳሙ ፯፥ ፰-፲፮::) የተባሉት ሲኾኑ፡ ከላይ የተጠቀሱት፡ የቀደሙት ስድስቱ ኪዳናት ታድሰው የተዋሃዱበትና ለዘለዓለም ጸንተው የሚኖሩበት፡

፯ኛውና የመጨረሻው፡ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ከቅድስት ድንግል ማርያም ተወልዶ፡ በተሰቀለበት፡ ቅዱስ ሥጋውና ባፈሰሰው ክቡር ደሙ ምልክትነት፡ የተገለጸው፡ "ኪዳነ ምሕረት" የተባለው አዲስ ኪዳን ነው፡፡ (ማቴ. ፳፮፥ ፳፮-፳፱::)

\+ + +

የእነዚህ ኪዳናት፡ የየግል መታወቂያ፡ ከላይ እንደሠፈረው፡ እውን በኾኑ፡ የተለያዩ ምልክቶች የተገለጸ ሲኾን፡ በሰውነት ገዝፈው የታዩት ደግሞ፡ ለፈጣሪያቸው ባላቸው እውነተኛ ፍቅር፡ እርሱን አምላካቸውን ባስደሰቱ ትሑታን ግለሰቦች ሕያው አካል ላይ ነው፡፡ እኒህ ግለሰቦች፡ በአካላዊውና በመንፈሳዊው አግጣጫ፡ በተለያዩ መልኮች የመጡባቸውን ታላላቅ ፈተናዎች፡ ብቻቸውን ተቋቁመው በማሸነፍ፡ በተጐናጸፉት የድል አክሊል፡ ከሰው ልጆች መካከል ብርቅ ኾነው ሊታዩና ከፈጣሪያቸው ከእግዚአብሔር ጋር፡ የየራሳቸውን ኪዳን፡ በነፍስ ወከፍ ሊካየዱ የቻሉ ገድለኞች ለመኾን በቅተዋል፡፡ እያንዳንዳቸውም፡ የሰውን ዘር በመወከል፡ የመለኮታዊው ልዩ ቃል ኪዳን ተዋዋይ ኾነው ለመመረጥ፡ በፊቱ ሞገስን በእውን ከማግኘታቸው አስቀድሞ፡ ለእርሱ ለእግዚአብሔር ያላቸው ፍቅር፡ እውነተኛ መኾኑ ሊረጋገጥ ስለሚገባ፡ እኒያ ፈተናዎች፡ እሳት ኾነው ሊያጠሩዋቸው፡ በየሰብእናቸው ላይ ነድደውባቸዋል፡፡

ከላይ የተዘረዘሩት፡ ሰባቱ ቅዱሳት ኪዳናት፡ የኢትዮጵያን እና የኢትዮጵያዊዉን/ዊቷን ህልውና፥ ሕይወትና ማንነት ያስገኙ፡ ሰባቱ ባሕርያት ናቸው፡፡ በሌላ አገላለጽ፡ ኢትዮጵያ ወይም ኢትዮጵያዊው/ዊቷ ማለት፡ እኒህ ሰባቱ ኪዳናት ናቸው! አዎን፥ እኒህ ሰባቱ ኪዳናት፡ ኢትዮጵያ ወይም ኢትዮጵያዊው/ዊቷ ማለት ናቸው፡፡ ያለእነዚህ ሰባቱ ኪዳናት፡ ወይም ከእነርሱ ውጪ በሚያደርግ፡ ሌላ የህልውና ሥርዓት ወይም ርእዮተ ዓለም፡ ኢትዮጵያ የምትባል አገር የለችም፤ ልትኖርም አትችልም፡፡ ወይም ኢትዮጵያዊ የሚባል ሰብአዊ ፍጡር ወይም ሕዝብ የለም፤ ሊኖርም ከቶ አይችልም፡፡

በዚህ መሠረትና ከዚህ የተነሣ፡ ይህች ኢትዮጵያ፡ እውነተኛዪቱ ኢትዮጵያ ብቻ ሳትኾን፡ እውነተኛዪቱ እስራኤል ጭምር፥ እኒህ ኢትዮጵያውያንም፡ እውነተኞቹ ኢትዮጵያውያን ብቻ ሳይኾኑ፡ እውነተኞቹ እስራኤላውያን ጭምር እንደኾኑ፡ የብሉዩንና የሐዲሱን ኪዳናት አጠቃልለው የያዙት ቅዱሳት መጻሕፍት፡ በዚያች በእግዚአብሔር የእውነት ቃል፡ ልዩ እውቅናን ሰጥተው፡ በማያወላውልና በማያዳግም ኹኔታ አጽድቀውታል፡፡

\+ + +

ኢትዮጵያውያን፡ በተከታታይነት የተፈጸሙትን፡ እኒህን ቅዱሳት ኪዳናት፡ ከመጀመሪያው እስከመጨረሻው፡ ማለትም፡ ከአዳምና ሔዋን የፍጥረት ዘመን አንሥቶ፡ በዘመነ ሥጋዌ፡ እስከኢየሱስ ክርስቶስና ድንግል ማርያም መገለጥ ድረስ፡ ያልተቆጠበና ያልተገደበ፥ ወደር የሌለውንም መሥዋዕትነት በመክፈል፡ በሙሉ ጠብቀዋቸው ኖረዋል፡፡

ኢየሱስ ክርስቶስ፡ የኢትዮጵያ አካላዊትና አማናዊት መገለጫ ከኾነችው፡ ከድንግል ማርያም፡ በሰውነት በተወለደ ጊዜ፡ እነዚህ ቅዱሳት ኪዳናት፡ በእርሱ ሥጋዌ፡ ፍጹም የኾነውን፡ አካላዊና አማናዊ ግዝፈት መቀዳጀታቸው ታወቀ! በዚህም፡ ከእግዚአብሔር የተነገሩት የትንቢት ቃላት ኹሉ፡ የመጨረሻውን ብቅዓት አግኝተው መፈጸማቸውና እግዚአብሔር፡ ለፍጥረቱ ያዘጋጀው መለኮታዊ ዕቅድ፡ ከተወጠነለት ግብ መድረሱ ተረጋገጠ፡፡

ይህ የኢትዮጵያውያን ትውፊት፡ ከላይ እንደተወሳው፡ "ሕያው ነው" የተባለበት ዓቢይና ልዩ ምክንያት አለው፡፡ ይኸውም፡ በቅዱሱ ኪዳን ውርስና ቅርስ ላይ የተመሠረተው፡ የኢትዮጵያውያን ትውፊት፡ ከትውልድ ወደትውልድ እየተላለፈ፡ ተጠብቆ የኖረው፡ እንዲያው በተለመደውና ተራ በኾነው፡ በግዑዙ ቍሳቍስ ላይ በሚቀረጸው ሰው-ሠራሽ ዘዴ ሳይኾን፡ በተለይ ለመለኮት ዘለዓለማዊ ሥራ፡ ሕያው መገለጫው በኾነው፡ በኢትዮጵያዊው ሰውነት በመኾኑ ነው፡፡

አዎን! በመጨረሻው ዘመን፡ የአዲሱ ኪዳን መሥዋዕት በኾነው፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ሥጋና ደም፡ ታድሶና ተጠናክሮ፡ ለዘለዓለማዊው ሕይወት የበቃው፡ ያ ኢትዮጵያዊ ሰውነት፡ ከአዳምና ሔዋን ጀምሮ፡ እስከዚህ እስከዛሬው ጊዜ ድረስ ለቆየው፡ ለሰባት ሺህ አራት መቶ ዘጠና ስድስት ዓመታት ያህል ለኾነው ዕድሜ፡ የእነዚህ ሰባት ቅዱሳት ኪዳናት መለኮታዊ ማኅደር በመኾን አገልግሏል፡፡

እንኳንስ ቀደም ብሎ፡ ባሁኑ ጊዜም ቢኾን፡ እግዚአብሔር፡ ከሰው ዘር ጋር ላደረጋቸው ቃል ኪዳናት፡ ሕያው ምስክሩ፡ በእርግጥ፡ ኢትዮጵያዊው ብቻ ኾኖ ይገኛል፡፡ ይህ እውነታ፡ በዐይነተኞቹ ኢትዮጵያውያን ሕይወት ላይ ገሃድ ኾኖ፡ ዛሬም ስለሚታይ፡ ትክክለኛነቱንና አማናዊነቱን ለማስተባበል ከቶ አይቻልም፡፡

እንዲህ እንደመኾኑና ማናቸውም እውነተኛ ክርስቲያን፡ ሊኾን እንደሚገባው ኹሉ፡ "ኢትዮጵያዊው ግለሰብ፡ የብሉዩንና የሐዲሱን ኪዳናት የያዙት፡ ቅዱሳት መጻሕፍት፡ ሥጋ ለብሰው፡ ሕያው የኾኑበት ሰብአዊ አካል ነው" ብለን አረጋግጠን እንናገራለን፡፡ ይህ፡ ለብፅዕና የሚያበቃው በረከት፡ ከረዥም ዘመናት በፊት፡ በነቢዩ ኤርምያስ ትንቢታዊ አንደበት ተነግሩዋል፡፡ ቃሉም እንዲህ ይላል፡-

**"'እነሆ፥ ከእስራኤልና ከይሁዳ ቤት ጋር አዲስ ቃል ኪዳን የምገባበት ወራት ይመጣል!' ይላል እግዚአብሔር፤ 'ከግብፅ አገር አወጣቸው ዘንድ፡ እጃቸውን በያዝኩበት ቀን፡ ከአባቶቻቸው ጋር እንደገባሁት ያለ ቃል ኪዳን አይደለም! እነርሱ በኪዳኔ አልጸኑምና፥ እኔም ቸል አልኋቸው!' ይላል እግዚአብሔር፡፡**

**"'ከእነዚያ ወራት በኋላ፡ ከእስራኤል ቤት ጋር የምገባው ቃል ኪዳን ይህ ነውና!' ይላል እግዚአብሔር፤ 'ሕጌን በልቡናቸው አኖራለሁ! በልባቸውም እጽፈዋለሁ! እኔም አምላክ እኾናቸዋለሁ! እነርሱም ሕዝብ ይኾኑኛል፡፡**

**"'እያንዳንዱ ሰው ባልንጀራውን፥ እያንዳንዱም ወንድሙን፡ 'እግዚአብሔርን እወቅ!፡ ብሎ አያስተምርም፤ ከታናሹ ጀምሮ እስከታላቁ ድረስ፡ ኹሉ ያውቁኛልና!' ይላል እግዚአብሔር፡፡ 'በደላቸውን እምራቸዋለሁና! ኃጢአታቸውንም፡ ከእንግዴህ ወዲህ አላስብምና!'"**

እነዚህን የትንቢት ቃላት፡ ራሱ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ በትምህርቶቹ ውስጥ አውስቷቸዋል፤ ሓዋርያው ጳውሎስም፡ ወደዕብራውያን በጻፈው መልእክቱ ውስጥ ጠቅሷቸዋል፡፡ በቅድሚያ፡ በበዓለ ሃምሣ ዕለት፡ በሓዋርያት፥ ተከታትሎም፡ "የአዲስ ኪዳኑ አቤሜሌክ" በተባለው፡ ኢትዮጵያዊ ጃንደረባ ላይ በወረደው የመንፈስ ቅዱስ ጸጋ፡ ይኸው የእግዚአብሔር ቃል፡ ደርሶ፡ የመፈጸሙን ምሥጢር አውቀናል፡፡ (ኤር. ፴፩፥ ፴፩-፴፬፡፡ ዮሐ. ፮፥ ፵፭፡፡ ዕብ. ፰፥ ፰-፲፪፡፡ የሓዋ. ፪፥ ፩-፬፤ ፰፥ ፳፮-፵፡፡)

\+ + +

እግዚአብሔር፡ በእኒያ፡ በሰባቱ ቅዱሳት ኪዳናት ተመሥርታ የታነጸችው መለኮታዊት መንግሥቱ፡ በእንዴት ያለ ኹኔታ፥ በምን ጊዜና በየትኛው ቦታ፡ በገሃድ ገዝፋ እንደምትሠራ፡ ብሩህና ቀጥተኛ በኾኑት፡ በእነዚህ ሕያዋን የነቢዩ ቃላት፡ ፍጹም ግልጽ አድርጎ አሳይቷል፡፡

እግዚአብሔር፡ ለዚህች መንግሥቱ አመሠራረትና አቋቋም፥ አመራርና አካኼድ፡ እጅግ የተራቀቁትና ውስብስብ የኾኑት፡ የሰው ልጆች፡ ድርጅታዊና ማኅበራዊ፥ ትምህርታዊና ንዋያዊ ሥርዓቶችና ጥበቦች አላስፈለጉትም፤ አዎን! እነዚህ ኹሉ፡ ሰው፡ ራሱን በራሱ፡ በሙስና (በብልሹነት) እንዲደመስስ እስከማድረግ የሚያደርሱ፡ ሕፀፅን (ጉድለትን) እና ስሕተትን፥ ድክመትንና ስስትን የተመሉ ናቸውና፡ አላስፈለጉትም፡፡

ዛሬ፡ በዚህ ቁሳዊ ዓለም፡ መልካሚቱን ኑሮ ለመኖር፥ ወደፊትም፡ ለሚመጧት ፍጽምት ዓለም ለመብቃት ይችሉ ዘንድ፡ የሰውን ልጆች፡ ወደእውነትና ወደሕይወት ልዕልና የምታደርሰው መንገዱ፡ የምትመራበትን ዘለዓለማዊ መርሓ ግብርና የምትሰጠውን ጠቃሚ አገልግሎት፡ በሥራ ላይ ለማዋል፡ እግዚአብሔር፡ እንደሰዎች መንግሥት፡ ጽሑፋዊ መመሪያን ወይም የሕግ አዋጅን፥ ወይም የገንዘብ ወጪ ድልድልንና ርስት ጉልትን፥ ወይም የሠለጠነ የሰው ኃይልንና የትምህርት መሣሪያን፥ ወይም መሠረታዊ የልማት አውታርንና ባለብዙ ዘርፍ የጽሕፈት ቤት ተቋምን፥ ወይም፡ አስገዳጅ የጦር ኃይል ያለውን፡ የሥራ አስፈጻሚ ባለሥልጣንን አልፈለገም፡፡

ኹሉን ማድረግ የማይሣነው፡ እርሱ፡ ኃያሉ እግዚአብሔር፡ የዘውድ መንግሥቱን፡ በምድር ላይ መሥርቶ ለማካኼድ ያስፈለገችው አንዲት ቅንጣት ነገር ብቻ ኾና ተገኘች! እርሷም፡ ህልውናዋና አምልኮዋ፡ በእውነትና በመንፈስ ላይ የተመሠረተ፡ **የዋህና ትሑት፥ ታማኝና ተነሳሒ የኾነች ሰብአዊት ልቦና ናት፡፡**

እግዚአብሔር፡ ያችን ልቦና ለማግኘት፡ ከዘመነ ፍጥረት አንሥቶ፡ በአዳምና ሔዋን፥ ከዚያም በልጅ ልጆቻቸው ሰውነት፡ ፍለጋውን ጀመረ፤ እነሆም፡ በተለይ ለቃል ኪዳኑና ለአገልግሎቱ በበቁት፡ በኖኅና ሚስቱ፥ በመልከ ጼዴቅ፥ በአብርሃምና ሣራ፥ በካህኑ ዮቶርና ሚስቱ፥ በሙሴና ሲጳራ፥ በዳዊትና ቤትሳባ፥ በሰሎሞንና ማክዳ ተያይዛ እየወረደችና እየተጠበቀች ኖራ፡ በመጨረሻ፡ በአማናዊዋ ሔዋን፡ በድንግል ማርያም ሰውነት ውስጥ፡ ለፍጹምነት በቅታ አገኛት! በእርሷም ማኅጸን፡ እግዚአብሔር ቃል፡ "አማናዊውና ዳግማዊው አዳም" ተብሎ፡ በኢየሱስ ክርስቶስ የሥጋዌ፡ አካል፡ በተዋሕዶ ከብሮ ተገለጸ! የዛሬው አዳም፡ ኢትዮጵያዊውና የዛሬዋ ሔዋን ኢትዮጵያዊቷም፡ ቅዱሱን ኪዳን፡ ከኢየሱስ ክርስቶስና ከድንግል ማርያም፡ በመንፈስ ቅዱስ ተረክበው፡ ይኸው፡ እስካሁን በባለአደራነት ጠብቀው ለማቆየት ችለዋል፡፡

አዎን! እግዚአብሔር፡ በትስብእት (መለኮት በተዋሃደው የሰውነት) ደም ታድሶ በጸናው፡ በቅዱሱ ኪዳን ሥርዓት የምትተዳደረውን፥ በልጁ፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ክህነታዊ ንጉሥነትና በድንግል ማርያም እናታዊ ንግሥትነትም የምትመራውን፡ ዘለዓለማዊት የዘውድ መንግሥቱን፡ ህልውናዋ፡ በቀደሙት ተከታታይ የዘመነ ብሉይ ቃል ኪዳናት እየለመለመ በቀጠለው፡ በዚች፡ ሕያውት በኾነችው፡ ኢትዮጵያዊት ዓለት ልቦና ላይ መሠረተ፡፡

እግዚአብሔር፡ ለሰው ዘር የሰጠውን፥ በኢትዮጵያውያንም ዘንድ፡ እስከዛሬ ጸንቶና ተጠብቆ የኖረውን፡ ይህን፡ ወሰንና ወደር የሌለውን፡ የተትረፈረፈ ጸጋ፡ በመላው ዓለም የሚኖሩ እውነተኞች ክርስቲያኖች ጭምር የሚጋሩት እንጂ፡ የኢትዮጵያውያን ብቻ አለመኾኑ፡ እዚህ ላይ ሊታወቅ ይገባል፡፡

\+ + +

የኢትዮጵያ ህልውናና የኢትዮጵያዊው ወይም የኢትዮጵያዊቷ ሕይወት፡ ኹለቱም፡ በእነዚህ በሰባቱ ቅዱሳት ኪዳናት ላይ በጽኑ ተመሥርተው፡ በተዋሕዶ የተሣሠሩ ናቸው፡፡ ይህንም፡ ከእነዚሁ ኪዳናት መንጭተውና በእነዚሁ ኪዳናት ለምልመው የሚታዩት፡ የኢትዮጵያውያን፡ የሃይማኖት፥ የባህልና የማኅበራዊ ኑሮ ሕይወታቸው ድርና ማግ ብቻ ሳይኾን፡ በትምህርት አሰጣጥ፥ በህብት ልማትና በሥነ መንግሥት አመራር ረገድ፡ በሥርዓት የሚከተሏቸው፡ ሕያዋን የኾኑት አምላካውያት ሕጎቻቸው ጭምር፡ በገሃድ አረጋግጠው ያሳያሉ፡፡

እንግዴህ፡ **"በውኑ ኢትዮጵያዊ፡ መልኩን፥ ወይስ፡ ነብር፡ ዝንጕርጕርነትን ሊለውጥ፡ ይችላልን?"** ተብሎ፡ በዚሁ የእግዚአብሔር ነቢይ አንደበት ስለተነገረው፡ ስለዚሁ **ኢትዮጵያዊነት፡** እውነታውን በዝርዝር ተረድቶ፡ እውነተኛውን እውቀት ለማግኘት፡ "ኢትዮጵያዊው፡ በማንነቱ ፍለጋ!"፥ "ኢትዮጵያ፡ የዓለሙ መፋረጃ!"፥ እና "Ethiopia: The Classic Case" በተባሉት መጻሕፍት፥ እንዲሁም፡ "ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊነት" በሚል ዓቢይ ርእስ ሥር፡ "አንደኛ"፥ "ኹለተኛ" እና "ሦስተኛ" የተባሉ ክፍሎች ባሉት፡ በአዲሱ መጽሐፍ ተከታታይ ዕትሞች ውስጥ የሠፈሩትን ሰፋፊ ሓተታዎች መመልከት ያስፈልጋል፡፡ (ኤር. ፲፫፥ ፳፫፡፡) እስከዚያው፡ ስለዚሁ ኢትዮጵያዊነት የሚያስረዱ፥ በቋሚ ጸሎትነት የሚያገለግሉ ጽሑፎች፡ ከዚህ እንደሚከተለው፡ በግእዝ፥ በኢትዮጵያኛና በእንግሊዝኛ ተዘጋጅተው፡ ለአንባብያን ቀርበዋል፡፡

# ጸሎተ ሃይማኖት፡ ዘኢትዮጵያውያን፡፡

<u>በግእዝ፦</u> ንሕነ ኢትዮጵያውያን፦

ነአምን፡ በአሐዱ አምላክ፡ እግዚአብሔር አብ፡ አኀዜ ኵሉ፥ ገባሬ ሰማያት ወምድር፡ ዘያስተርኢ፥ ወዘኢያስተርኢ፡፡

ወነአምን፡ በእግዚአብሔር ወልድ፡ አሐዱ እግዚእ፥ ወልደ አብ ዋህድ፥ ዘህልው ምስሌሁ፡ እምቅድመ ይትፈጠር ዓለም፤ ውእቱ ኢየሱስ ክርስቶስ፥ ብርሃን ዘእምብርሃን፥ አምላክ ዘእምአምላክ ዘበአማን፤ ዘተወልደ ወአኮ ዘተገብረ፥ ዘዕሩይ ምስለ አብ በመለኮቱ፤ ዘቦቱ ኵሉ ኮነ፤ ወዘእንበሌሁሰ አልቦ ዘኮነ፥ ወኢምንትኒ፥ ዘበሰማይኒ፥ ወዘበምድርኒ፡፡

ዘበእንቲአነ ለሰብእ፥ ወበእንተ መድኃኒትነ፡ ወረደ እምሰማያት፤ ተሰብአ ወተሠገወ፡ በግብረ መንፈስ ቅዱስ፡ እማርያም እምቅድስት ድንግል፤ በነሢአ ሥጋ እምሥጋሃ፥ ወነፍስ እምነፍሳ፡ ኮነ ብእሴ ፍጹመ፡፡ በመዋዕለ ጲላጦስ ጴንጤናዊ፡ ተሰቅለ፥ ወሓመ፥ ወሞተ፤ ወተቀብረ በእንቲአነ፡፡ ወተንሥአ እሙታን፡ አመ ሣልስት ዕለት፡፡ ዐርገ በስብሓት ውስተ ሰማያት፡፡ ወነበረ በየማነ አቡሁ፥ በመንበሩ ዘበዕሪና፡፡ ዳግመ ይመጽእ በስብሓት፤ ይኰንን ሕያዋነ ወእሙታነ፡፡ ወአልቦ ማኅለቅት ለመንግሥቱ፡፡

ወነአምን፡ በእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ፡፡ ውእቱ መንፈሰ ጽድቅ፥ ማኅየዊ ዘበአማን፥ ዘሠረጸ እምአብ፥ ዘንሰግድ ሎቱ ወንሰብሖ፡ ምስለ አብ ወወልድ፥ ወዘነበበ በነቢያት፥ ዘወረደ ላዕለ ሓዋርያት፥ ወጺጋሁ ዘመልዓ ዓለም፡ በቤዛ መስቀሉ ለኢየሱስ ክርስቶስ፡፡

ወነአምን፡ በአሓቲ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን፡ እንተ ይእቲ፡ ዘመሠረታ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ እምጥንት፥ በኪዳነ ልቦና ዘአበው ቀደምት፥ ወዘአጽንዓት በቃለ ነቢያት፥ ወዘፈጸማ በላዕለ ኵሉ ጉባዔ ዘሓዋርያት፡፡ በውስቴታ ያቄርቡ ካህናት፡ መሥዋዕተ ሥጋሁ ቅዱሰ፥ ወደሞ ክቡረ ለኢየሱስ ክርስቶስ፤ ወባቲ ይትዌከፉ ምእመናን፡ ጺጋ መንፈስ ቅዱስ ዘዘዚአሁ፡፡

ወነአምን፡ በአሓቲ ጥምቀት፥ ለሥርየተ ኃጢአት፡፡

ወነአምን፡ በትንሣኤ ሙታን፤ ወሕይወተ ዘይመጽእ፡፡ ለዓለመ ዓለም፤ አሜን፡፡

# ጸሎተ ኪዳነ ቃል፡ ዘኢትዮጵያውያን፡፡

ንሕነ ኢትዮጵያውያን፦

ነአምን በኢትዮጵያውናን፡ ዘኪዳን ቅዱስ፥ ህልው በዓቂበ ቃላት ኪዳናውያት፥ እለ ወሀቦሙ እግዚአብሔር፡ ለውሉደ ሰብእ፡፡

አምላክነ፡ ሣረረ ዝንቱ ሰብእና ኢትዮጵያዊ፡ በኪዳነ ልቦና፡ በዘኮነ እምሥርዓተ ከብካብ፡ ዘአዳም ወሔዋን፡ በዘመነ አበው ቀዳማዊ፤ ወመትሎሁ፡ አዕረጎ ለዝ ሕንፃ፡ በቀስተ ደመናሁ ለኖኅ፥ ወበቍርባኑ ዘመልከ ጼዴቅ፥ ወበግዝረቱ፡ ዘአብርሃም፤ ወበዘመነ ሕግ ማእከላይ፡ ነደቆ ማኅፈዱ፡ በጽላተ ሙሴ፥ ወበመንበረ ዳዊት፡ ዘግህደ በፅምረተ አሥራወ ዘርያሙ ለንግሥት ማክዳ ኢትዮጵያዊት፥ ወለንጉሥ ሰሎሞን እሥራኤላዊ፡ ከመ ያስተሰነአዎ ኵለንታሁ፡ በኪዳነ ኦሪት፤ ወእምድኅረ አጽንዖቱሰ፡ በሥጋሁ ወደሙ ለኢየሱስ ክርስቶስ ወልዱ፡ ዘተወልደ እምድንግል ማርያም፡ እንተ ሠረፀት እምዛቲ ሥርው ምልዕት፡ አስተቄጸሎ አክሊል ዘለዓለም፡ በፍጻሜ ዘመን ዘሕይወት፡ በኪዳነ መንፈስ ቅዱስ፡፡ በእንተዝ፡ ነአምን፡ ከመ ይእቲ ኢትዮጵያ፡ መንግሥተ እግዚአብሔር፡ እንተ ገዝፈት በሰብእናሁ ለኢትዮጵያዊ፡ ዘኪዳን ቅዱስ፡ እንዘ በኀቤሁ የኀብሩ፡ ቤተ ሕዝባ፥ ወቤተ ክህነታ፥ ወቤተ ምልክናሃ፡ በአሠረ ተዋሕዶ፡፡

*ንሕነ፡ እለ ተሠየምነ “ክርስቲያን”፡ በስመ ዚአሁ፡ ዘተብህለ “ክርስቶስ”፡ ነአምን፡ ከመ ውእቱ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ካህንነ ወንጉሥነ ዘለዓለም፡ በሢመቱ ለመልከ ጼዴቅ ኢትዮጵያዊ፡ ዘአስተርአየ በመዋዕል ቀዳማዊ፡ ወዘኮነ አርአያሁ ለክርስቶስ፡ በልደቱ፡ ዘኮነ፡ እምትሥልስተ ዘርዕ፡ ዘእምአንጋደ ሴም፥ ወካም፥ ወያፌት።*

*ንሕነ፡ እለ ተሠየምነ “ኢትዮጵያውያን” በስመ ዚአሃ ዘተብህለት “ኢትዮጵያ”፡ ነአምን፡ ከመ ይእቲ ድንግል ማርያም፡ እመ ሕያዋን አማናዊት፥ ወታቦተ ጽዮን ዘለዓለማዊት፥ ወንግሥተ ሰማያት ወምድር፡ በዘወሊዶታ ለአምላክ።*

*ነአምን፡ በቀስተ ደመና፡ ዘተሠርገወ በሠለስቱ ዓበይት ኅብረ ቀለማት፡ ዘውእቶሙ ሐመልሚለ፥ ወወርቀ፥ ወቀይሐ፡ ዘተውህበ ለነ እምእግዚአብሔር፡ እንተ በኀበ ኖኅ፡ ከመ ውእቱ ይኩነነ፡ ትእምርተ ኪዳን ዘለዓለም።*

*ነአምን፡ በማኅተምነ ዘለዓለም፡ ዘረከብነ እምአምላክነ፡ ወበዘውእቱ ዘተነግረ በእንተ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ መፈጽም ለኪዳኑ ቅዱስ፡ በዝንቱ ቃል ዘመለኮት፡ እንዘ ይብል፡* ***“ሞአ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ”*** *፥ ወበቃለ ትንቢት፡ ዘተነግረ፡ በእንተ ማርያም ድንግል፡ እንዘ ይብል፡* ***“ኢትዮጵያ ታበጽሕ እደዊሃ ኀበ እግዚአብሔር”*** *።*

*ነአምን፡ ከመ ንሕነ፡ ወራስያነ መንግሥቱ ወላእካኒሁ ለእግዚአብሔር፡ በእንተ ወልድናነ፡ በዘውእቱ ዘተከለልነ በክብረ ልደት እምእግዚአብሔር በመንፈስ፡ እንበይነ ጸጋሁ ዘኪዳኑ ቅዱስ።*

*ነአምን፡ ከመ ብነ ይደልወነ፡ ንሄሉ በንስሓ እንበለ ፅርዓት፡ ለሥርየተ ኃጢአት፥ ወበተመጥዎተ ሥጋሁ ወደሙ ለክርስቶስ፡ ለአጽንዖተ ዝንቱ ወልድናነ፥ ወለትውክልተ ውርስናነ ዘመንግሥቱ፥ ወለዝልፈተ ተልእኮትነ ንጹሕ።*

*ነአምን፡ ከመ ውእቱ ሃይማኖትነ ዘኢትዮጵያውና፡ ገሃደ ይወጽእ፥ ወቅድስናሁ ይትአወቅ፡ በምግባሪነ ዘኢትዮጵያውና፡ ዘንፈጽም በተዋሕዶተ ፍቅርነ ለኢየሱስ ክርስቶስ፥ ወለድንግል ማርያም።*

*ነአምን፡ ከመ እግዚአብሔር ውእቱ፡ ዘጸሓፈ ኢትዮጵያውናነ ዘኪዳን ቅዱስ፡ በልቦናነ፥ ወመሀረነ፥ ወረሰየነ፡ ንዕቀብ በሀልዎትነ በእንተ ቃለ ኪዳኑ። ለዓለም ዓለም፤ አሜን።*

# *<u>የኢትዮጵያውያን፡ የሃይማኖት ጸሎት።</u>*

***<u>በኢትዮጵያኛ፡-</u>***

*እኛ ኢትዮጵያውያን፡-*

*ኹሉን በያዘ፥ ሰማይንና ምድርን፥ የሚታየውንና የማይታየውን በፈጠረ፡ አንድ አምላክ በሚኾን፡ በእግዚአብሔር አብ እናምናለን።*

*ዓለም ሳይፈጠር፡ ከእርሱ ጋራ በነበረ፥ አንድ የአብ ልጅ፥ አንድ ጌታ በሚኾን፡ በእግዚአብሔር ወልድም እናምናለን። እርሱም፡ ከብርሃን የተገኘ ብርሃን፥ ከእውነተኛ አምላክ የተገኘ አምላክ፥ የተወለደ እንጂ ያልተፈጠረ፥ በመለኮቱ፡ ከአብ ጋራ የሚተካከል፥ ኹሉ በእርሱ የኾነው ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። በሰማይ ካለው፥ በምድርም ካለው፡ ያለእርሱ፡ ምንም ምን የኾነ የለም። ስለእኛ ስለሰዎች፥ እኛን ለማዳን፡ ከሰማይ ወረደ፤ በመንፈስ ቅዱስ ግብር፡ ከቅድስት ድንግል ማርያም፡ ከሥጋዋ ሥጋ፥ ከነፍሷ ነፍስ ነሥቶ፡ ፍጹም ሰው ኾነ። በጴንጤናዊው ጲላጦስ ዘመን፡ ስለእኛ መከራን ተቀበለ። ተሰቀለ። ሞተ። ተቀበረ። በሦስተኛውም ቀን፡ ከሙታን ተለይቶ ተነሣ። በክብር በምስጋና ወደሰማይ ዐረገ። በአባቱም ቀኝ፡ በዙፋኑ ተቀመጠ። ዳግመኛም፡ በሕያዋንና በሙታን ለመፍረድ፡ በምስጋና ይመለሳል። ለመንግሥቱ ፍጻሜ የለውም።*

*በእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስም እናምናለን። እርሱም፡ ሕይወትን የሚሰጥ፥ ከአብ የሠረፀና በነቢያት አድሮ የተናገረው፥ በሐዋርያት ላይ የወረደውና በኢየሱስ ክርስቶስ ቤዛነት፡ ዓለሙን በጸጋው የሞላው፡ ቅዱሱ የእውነት መንፈስ ነው። ለእርሱም፡ ከአብና ከወልድ ጋራ፡ በአንድነት እንሰግድለታለን፤ እናመሰግነዋለን።*

ኢየሱስ ክርስቶስ፡ በአበው ልቦና በመሠረታት፥ በነቢያት ቃል ባጸናትና በሐዋርያት ጉባዔ በፈጸማት፥ የእርሱ ሥጋና ደም፡ ለመሥዋዕትነት በሚቀርብባትና የመንፈስ ቅዱስ ጸጋዎች በሚሰጡባት፡ በአንዲት ቅድስት ቤተ ክርስቲያን እናምናለን።
ኃጢአት በሚሠረይባት፡ በአንዲት ጥምቀት እናምናለን።
በሙታን ትንሣኤ፥ በሚመጣውም ሕይወት እናምናለን። ለዘለዓለሙ፥ አሜን።

## የኢትዮጵያውያን፡ የቃል ኪዳን ጸሎት።

እኛ ኢትዮጵያውያን፦

እግዚአብሔር ለሰው ልጆች፡ የሰጣቸውን ቃል ኪዳናት፡ ጠብቆ በኖረው፡ በቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነታችን እናምናለን።

አምላካችን፡ ይህን ኢትዮጵያዊ ሰውነት፡ **በመጀመሪያው የአበው ዘመን፡** በአዳምና ሔዋን ሥርዓተ ጋብቻ፡ **በኪዳነ ልቦና መሠረተው፤** ከዚያም፡ በኖኅ ቀስተ ደመና፥ በመልከ ጼዴቅ ቁርባንና በአብርሃም ግርዛት፡ ገንብቶ አሳደገው፤ **በመካከለኛውም የሕግ ዘመን፡** በሙሴ ጽላትና በዳዊት ዙፋን አዋቅሮ፥ የኢትዮጵያዊቷን ንግሥት፡ የማክዳንና የእስራኤላዊዉን ንጉሥ፡ የሰሎሞንን የዘር ሓረጎች በማዋሓድ፡ በኪዳነ ኦሪት አከናወነው፤ **በመጨረሻውም የሕይወት ዘመን፡** ከዚህ ምሉእ ትውልድ ከተገኘችው፡ ከድንግል ማርያም በተወለደው ልጁ፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ሥጋና ደም አጽንቶና ዘለዓለማዊዉን ዘውድ አቀዳጅቶ፡ በኪዳነ መንፈስ ቅዱስ ፈጸመው። ኢትዮጵያ፡ እንዲህ በቀጠለው፡ በቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊው ሰውነት፡ ቤተ ሕዝቧን፥ ቤተ ክህነቷንና ቤተ ምልክናዋን አንድ አድርጋ የኖረች፡ የእግዚአብሔር መንግሥት እንደኾነች እናምናለን።

እርሱ፡ "ክርስቶስ" ተብሎ፡ እኛን "ክርስቲያን" ያሰኘን፡ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ በቀደመው ዘመን፡ ምሳሌው ኾኖ በተገለጠው፡ በመልከ ጼዴቅ ኢትዮጵያዊነትና ሹመት፡ ከሴም፥ ከካምና ከያፌት ዘሮች ተወልዶ፡ የዘለዓለም ካህናችንና ንጉሣችን እንደኾነ እናምናለን።

እርሷ "ኢትዮጵያ" ተብላ፡ እኛን "ኢትዮጵያውያን" ያሰኘችን፡ ድንግል ማርያም፡ አምላክን በመውለዷ፡ አማናዊቷ የሕያዋን እናትና ዘለዓለማዊቷ ታቦተ ጽዮን፥ የሰማይና የምድር ንግሥትም እንደኾነች እናምናለን።

አረንጓዴ ብጫ ቀይ የኾነው፡ የቀስተ ደመና ምልክት፡ በኖኅ አማካይነት፡ ከእግዚአብሔር የተቀበልነው፡ የዘለዓለም ሰንደቅ ዓላማችን እንደኾነ እናምናለን።

የቅዱሱ ኪዳን ፍጻሜ ለኾነው፡ ለኢየሱስ ክርስቶስ የተነገረው፡ "ሞአ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ" የሚለው፡ መለኮታዊ ቃልና ለድንግል ማርያም የተነገረው፡ "ኢትዮጵያ ታበጽሕ እደዊሃ ኀበ እግዚአብሔር" የሚለው ትንቢታዊ ቃል፡ ከአምላካችን ያገኘነው፡ የዘለዓለም ማኅተማችን እንደኾነ እናምናለን።

በቅዱሱ ኪዳን ጸጋ፡ ከእግዚአብሔር በመንፈስ፡ የመወለድን ክብር ስላገኘን፡ በዚህ ልጅነታችን፡ የእግዚአብሔር መንግሥት ወራሾችና አገልጋዮች እንደኾንን እናምናለን።

ይህን ልጅነታችንን፡ አጽንተን ለመጠበቅ፥ የመንግሥቱ ወራሽነታችንን ለማረጋገጥና ንጹሕ አገልግሎታችንን ለመቀጠል፡ ኃጢአታችንን ዘወትር፡ በንስሓ እያጠራንና የክርስቶስን ሥጋና ደም እየተቀበልን መኖር እንዳለብን እናምናለን።

የኢትዮጵያዊነት ሃይማኖታችን፡ በይፋ የሚገለጠውና ተለይቶ የሚታወቀው፡ በኢየሱስ ክርስቶስና በድንግል ማርያም ፍቅር ኾነን በምንፈጽመው፡ የኢትዮጵያዊነት ምግባራችን እንደኾነ እናምናለን።

የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነታችንን፡ በየልቦናችን ጽፎ ያስተማረን፥ ጠብቀነው እንድንኖር ያደረገም፡ እንደቃል ኪዳኑ፡ እግዚአብሔር እንደኾነ እናምናለን። ለዘለዓለሙ፤ አሜን።

## ጸሎተ ስባሔ ለእግዚአብሔር፡ እለ ያቀርቡ ሎቱ፡ ኢትዮጵያውያን፡፡

በግእዝ፡-

ኦ አቡነ እግዚአብሔር! ንሴብሐከ፡ በእንተ ዘተወከፍከ ዝንቱ ጸሎትነ፡ በቤዝዎቱ ለወልድከ፡ ዘመሀረነ ለሊሁ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ እንዘ ይብል፡ "**አንትሙሰ ሶበ ትጼልዩ፡ ከመዝ በሉ፡- 'አቡነ ዘበሰማያት! ይትቀደስ ስምከ፤ ትምጻእ መንግሥትከ፤ ወይኩን ፈቃድከ፥ በከመ በሰማይ፥ ከማሁ በምድር፤ ሲሳየነ፥ ዘለለዕለትነ፥ ሀበነ ዮም፤ ሕድግ ለነ፥ አበሳነ፥ ወጌጋየነ፥ ከመ ንሕነኒ ንሕድግ፡ ለዘአበሰ ለነ፤ ኢታብአነ እግዚኦ፡ ውስተ መንሱት፤ አላ አድኅነነ፥ ወባልሃነ እምኲሉ እኩይ፤ እስመ ዚአከ፡ ይእቲ መንግሥት፥ ኃይል ወስብሓት፤ ለዓለመ ዓለም!**'" ወበእንተ፡ ዘአብዛኀከ ለነ፡ ኂሩትከ፤ ወዘገበርከ ለነ፡ ምሕረትከ፥ ወዘፈጸምከ ለነ፡ ፍቅርከ፥ ወዘወሀብከነ ጸጋከ፡ ለከዊነ ነፍስነ ወሥጋነ፡፡

ወረደ ለነ፡ ጸጋ መንፈስ ቅዱስ፡ ውስተ ኲሉ ዓለም፡ በምክንያተ ቤዛ ወልድከ መድኅን፡ ዘተወልደ እምቅድስት ድንግል ማርያም፡፡ በእንተዝ፡ ኮነ ይእዜ፡ ዘትሄሉ አንተ፡ በምድር፥ አኮ በሰማይ ባሕቲቱ፡፡ ወዓዲ፡ ተቀደሰ ስምከ፡ በምድር፡፡ ወመጽአት መንግሥትከ፡፡ ፈቃድከ፡ ዘኮነ በሰማይ፥ ከማሁ፡ ኮነ፡ በምድርኒ፡፡

አስተዳለውከ በሥነ ፍጥረት፡ ምግበ ሥጋነ፡ ዘይበቍዕ ለመፍቅደ ኲሉ ሀልዎትነ፥ ወአኮ ሲሳይ፡ ዘለለዕለትነ ባሕቲቱ፡፡ ወመጦከነ በኲሉ ጊዜ፡ ሥጋ ወልድከ ቅዱስ፥ ወደሞ ክቡረ፡ ዘኮነ ለነ፡ መድኃኒት፥ ወምግበ ነፍስ፡ ዘይረስየነ ሕያዋን ዘለዓለም፤ ወበውእቱሰ፡ ደምሰስከ፥ ወኃደግከ ለነ፡ ኲሎ ኃጢኣተነ፥ ወአበሳነ፡ ግሙራ፥ ወኢማእዜ፤ ወከማሁ አባሕከነ፡ ከመ ንሕነኒ ንኅድግ ኲሎ፡ ለዘአበሰ ለነ፡፡

ወዐልዓልከነ በልደተ መንፈስ ቅዱስ ዘጥምቀት፥ ወጸጋ ዘንስሓ፡ በዘውእቱ በጻሕነ፡ ከመ ንኩን ውሉድከ፥ ወአዋልድከ፡፡

ወአውጻእከነ እመንሱት ዘዘዚአሁ፤ ወአድኃንከነ እምኲሉ እኩይ፤ ወሞዕክዎ ለዲያብሎስ፥ ወአሰሰልከ ለሞት፤ ወበእንተ ዝንቱ፡ አሠለጥከነ ንሄሉ፡ በሕይወተ ትንሣኤከ፡፡

ኦ እግዚኦ! ንሴብሓከ ወትረ፡ በእንተ ኂሩትከ፥ ወምሕረትከ፥ ወፍቅርከ፥ ወጸጋከ፡ ዘአወፈይከነ፡ በዘኢይትከሃል ይትነገር መጠኑ፤ ወዓዲ፡ በእንተ ዘትሁበነ፡ ኲሎ ዘንፈቅድ፡ እንዘ አኮ ዘንሰአለከ፡፡

ንጸንሕ፡ በከመ አሰፈውከነ፡ ለምጽአተ ዛቲ መዋዕል፡ እንተ ባቲ፡ ትኴንን መንግሥትከ አማናዊት፡ ዘንጉሥነ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ዘተብህለ፡ "ሞአ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ"፤ እለ ንሄሉ ንሕነ፡ ይእዜ፡ በውስቴታ፡ ከመ ትትረአይ ወትሰፍን በገሃድ፡ በዝንቱ ዓለም፡ እምድኅረ ትሤርዎሙ ለእከይ፥ ወለኃጢኣት፥ ወለሞት፡፡

እስመ ለከ፡ ኃይል፥ ወስብሓት፥ ወመንግሥት፤ ይእዜኒ፥ ወዘልፈኒ፥ ወለዓለም ዓለም፤ አሜን፡፡

## ጸሎተ ሱላሜ፡ ለድንግል ማርያም፡ እለ ያቀርቡ ላቲ፡ ኢትዮጵያውያን፡፡

ኦ ማርያም እምነ! ንብለኪ፡ "ሰላም ለኪ!" በሰላመ ቅዱስ ገብርኤል መልአክ፡፡ ድንግል፡ በሕሊናኪ፤ ወድንግል፡ በሥጋኪ፡፡ ይደልወኪ ዝ ሱላሜ፤ እስመ ኮንኪ አንቲ፡ እሙ ለእግዚአብሔር ጸባዖት፡ በእንተ ዛቲ ንጽሓ ባሕርይኪ፡፡

አንቲ ውእቱ ሔዋን ቅድስት፥ ወቡርክት፡ እምኲሎን አንስት፡ በእንተ ዘአሥረፀ ማሕፀንኪ፡ ፍሬሁ ዘዕፀ ሕይወት፡ በዘውእቱ ኮነ አዳምሁ ቅዱሰ፡፡ ተፈሥሒ! ኦ ንግሥትነ፡ በሰማይ ወበምድር! እስመ ዘተወደስኪ ጥንት፡ በአፈ ነቢያት፡ እንዘ ይብሉኪ፡ "**ኢትዮጵያ ታበጽሕ እደዊሃ ኀበ እግዚአብሔር!**"፥ ወንሕነኒ፡ በዘሀልዎትነ፡ እንዘ ንብለኪ፡ "**እምነ ጽዮን!**"፡፡ ንዌድሰኪ ወትረ፡ እንዘ ንብል፡ "ብፅዕት አንቲ፡ ምልዕተ ጸጋ!"፡ እስመ ዐተበ እግዚአብሔር፡ ኪዳኖ ዘምሕረት፡ ለዓለመ ዓለም፡ በዘአጥረየኪ አንቲ፡ ለምክንያተ ድኅነትነ፡፡

ነአምን፡ ከመ ኢተግሕሠ ክመ እምኔነ፡ ማሕፀንተኪ፡ በአምጣነ እንተ ኢተግሕሠ፡ እምፍቁር ወልድኪ፤ እስመ አንቲ ውእቱ እምነ፡ ዘምሕፀና፥ ወንሕነ፡ ውሉድኪ፥ ወአዋልድኪ፡ ዘምሕፅና፡ በቃለ አማሕፀኖ ዘወልድኪ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ አምላክነ፥ ወመድኃኒነ።

ነአኵቶ ለእግዚአብሔር ልዑል፡ አቡነ ኄር፡ በእንተ ዛቲ ኂሩቱ፡ ዘገብረት ለነ።

ለዓለመ ዓለም፤ አሜን።

## <u>ለእግዚአብሔር የሚያቀርቡት፡ የኢትዮጵያውያን፡ የምስጋና ጸሎት።</u>

<u>በኢትዮጵያኛ፡-</u>

አባታችን እግዚአብሔር ሆይ! "እናንተ ስትጸልዩ፡ **'አቡነ ዘበሰማያት! ይትቀደስ ስምከ፤ ትምጻእ መንግሥትከ፤ ወይኩን ፈቃድከ፥ በከመ በሰማይ፥ ከማሁ በምድር፤ ሲሳየነ፥ ዘለለዕለትነ፥ ሀበነ ዮም፤ ሕድግ ለነ፥ አበሳነ፥ ወጌጋየነ፥ ከመ ንሕነኒ ንሕድግ፡ ለዘአበሰ ለነ፤ ኢታብአነ እግዚኦ፡ ውስተ መንሱት፤ አላ አድኅነነ፥ ወባልሃነ እምኵሉ እኩይ፤ እስመ ዚአከ ይእቲ መንግሥት፥ ኃይል ወስብሓት፤ ለዓለመ ዓለም!'** በሉ!" ብሎ፡ ልጅህ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ያስተማረንን ጸሎታችንን፡ በእርሱው ቤዛነት ተቀብለህ፡ ለነፍሳችንና ለሥጋችን፡ ቸርነትህን አበረከትክልን፤ ምሕረትህን አደረግህልን፤ ፍቅርህን ፈጸምክልን፤ ጸጋህንም ሰጠኸን። ስለዚህ እናመሰግንሃለን።

ከቅድስት ድንግል ማርያም፡ በተወለደው ልጅህ መድኃኒትነት፡ የመንፈስ ቅዱስ ጸጋ፡ በዓለሙ ኹሉ ወረደልን። ስለዚህ፡ በሰማይ ብቻ ሳይኾን፡ ዛሬ በምድርም የምትኖር ኾንህ። ስምህ፡ በምድርም ተቀደሰ። መንግሥትህም መጣችልን። በሰማይ የኾነው ፈቃድህ፡ በምድርም እንዲሁ ኾነ።

የዕለት እንጀራችንን ብቻ ሳይኾን፡ በዕድሜያችን ኹሉ የሚያስፈልገንን ምግበ ሥጋ፡ በሥነ ፍጥረት አዘጋጀህልን። ለዘላለም ሕያዋን የሚያደርገንን፥ መድኃኒትና ምግበ ነፍስ የኾነንን፡ የልጅህን ቅዱስ ሥጋና ክቡር ደም፡ ለዘወትር ሰጠኸን። በእርሱም፡ ኃጢአታችንንና በደላችንን ኹሉ፡ ለመቼውም ጊዜ ደምስሰህ፡ ፈጽመህ ይቅር አልኸን። እኛም የበደሉንን ኹሉ፡ እንዲሁ ይቅር እንድንል አስቻልኸን።

የአንተ ልጆች ለመኾን የምንበቃበትን፡ የጥምቀትን ልደትና የንስሓን ጸጋ አደልኸን።

ከማናቸውም ፈተና አውጥተኸንና ከክፉው ኹሉ አድነኸን፥ ዲያብሎስንና ሞትንም ድል አድርገህ፡ በትንሣኤህ ሕይወት ለመኖር አበቃኸን።

ጌታ ሆይ! ሊነገር ስለማይቻል ቸርነትህና ምሕረትህ፥ ፍቅርህና ጸጋህ፥ እንዲሁም የሚያስፈልገንን ኹሉ፡ ሳንለምንህ ስለምትሰጠን፡ ዘወትር እናመሰግንሃለን።

"**ሞአ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ**" በተባለው፡ በንጉሣችን በኢየሱስ ክርስቶስ፡ ዛሬ የምንኖርባት፡ የእውነት መንግሥትህ፡ ክፋትን፥ ኃጢአትንና ሞትን፡ ፈጽማ አጥፍታ፡ ለግዙፉ ዓለም፡ በገሃድ የምትገለጥበትንና በይፋ የምትሰፍንበትን ጊዜ፡ እንደተስፋ ቃልህ እንጠብቃለን።

ኃይልና ምስጋና፥ መንግሥትም ያንተ ናቸው፤ ዛሬም፥ ዘወትርም፥ ለዘለዓለሙ፤ አሜን።

## ለድንግል ማርያም የሚያቀርቡት፡ የኢትዮጵያውያን፡ የሰላምታ ጸሎት፡፡

እናታችን ማርያም ሆይ! በመልአኩ በቅዱስ ገብርኤል ሰላምታ፡ "ሰላም!" እንልሻለን፡፡ በአሳብሽ ድንግል ነሽ፤ በሥጋሽም ድንግል ነሽ፡፡ በዚህ የንጽሕና ባሕርይሽ፡ የአሸናፊው የእግዚአብሔር እናት ኾነሻልና፡ ሰላምታ ላንቺ ይገባል፡፡

ማሕፀንሽ፡ የሕይወት ዛፍ ፍሬ የኾነውን፡ ቅዱሱን አዳም ስላስገኘ፡ አንቺ፡ ከሴቶች ኹሉ ተለይተሽ፡ የተባረክሽ፡ ቅድስቲቱ ሔዋን ነሽ፡፡ ቀድሞ በነቢያት፡ "**ኢትዮጵያ ታበጽሕ እደዊሃ ኀበ እግዚአብሔር**" የተባልሽ፥ እኛም፡ "**እምነ ጽዮን**" ስንልሽ የኖርን፡ በሰማይና በምድር፡ ንግሥታችን ሆይ! ደስ ይበልሽ፡፡

እግዚአብሔር አንቺን፡ የድኅነታችን ምክንያት አድርጎ፡ ኪዳነ ምሕረቱን ለዘለዓለም ፈጽሟልና፡ "ጸጋን የተመላሽ፡ ብፅዕት ነሽ" እያልን፡ ዘወትር እናወድስሻለን፡፡

በአምላካችንና በመድኃኒታችን፡ በኢየሱስ ክርስቶስ፡ አንቺ ለእኛ፡ የአደራ እናታችን፥ እኛም ለአንቺ፡ የአደራ ልጆችሽ ነንና፡ ከተወደደው ልጅሽ፡ ያልተለየው እናትነትሽ፡ ከእኛም፡ ምንጊዜም እንደማይለየን እናምናለን፡፡ ይህን ያደረገ፡ ቸሩ አባታችን፡ ልዑል እግዚአብሔርን እናመሰግነዋለን፡፡ ለዘለዓለሙ፤ አሜን፡፡

## ለእግዚአብሔር የሚያቀርቡት፡ የኢትዮጵያውያን ምስጋና፡-

**በመዝሙር፡፡**

አባታችን ሆይ! የምትኖር በሰማይ፤
መንግሥትህ በስምህ፡ ሰፈነች በእኛ ላይ፡፡
        በሰማይ የጸናች፡ ሕያው ፈቃድህ፤
        ተፈጸመች በምድር፡ በሥግው ቃልህ፡፡
ፍቅርህ ለምግባችን፡ ፍጥረትን ያስገኘች፤
በደልን ደምስሳ፡ ዕርቅን መሠረተች፡፡
        ጌታ ሆይ! አዳንከን፡ ከሞት ከፈተና፤
        በልጅህ ቤዛነት፡ በትንሣኤው ፋና፡፡
ኃይልና ምስጋና፡ ጸንተው ለመንግሥትህ፤
አበቃኸን እኛን፡ ለቅዱስ ኪዳንህ፡፡

## ኢትዮጵያውያን፡ ለድንግል ማርያም የሚያቀርቡት ሰላምታ፡-

**በመዝሙር፡፡**

እናታችን ሆይ! ማርያም ድንግል፤
ሰላም እልሻለሁ፡ በገብርኤል ቃል፡፡
        በሥጋ አካልሽ፡ ደግሞም በሕሊና፤
        ባሕርይሽ ኾነ፡ ፍጹም ድንግልና፡፡
ላሸናፊው ጌታ፡ ለእግዚአብሔር እናት፤
ማቅረብ ይገባናል፡ ሰላምታን በምነት፡፡
        ከሴቶች መካከል፡ ባለሽ ቅድስና፤
        ማኅፀንሽ አፈራ፡ የሕይወትን መና፡፡
ደስ ይበልሽ አንቺ፡ ያምላክ ባለጸጋ፤
አቅርቢን ከልጅሽ፡ ደሙ ኾኖን ዋጋ፡፡

# የኢትዮጵያውያን፡ የቅዱሱ ኪዳን መዝሙር።

፩. ሃሌ ሉያ ለአብ፡ ለሰማይ አባታችን፤
ስብሐት ለእግዚአብሔር ወልድ፡ ካህን ንጉሣችን፤
ለመንፈስ ቅዱስም፡ ጸጋ ሕይወታችን፤
አቅርበናልና፡ በዝርጉ እጃችን፤
ጌታ ሆይ ተቀበል፡ ይኸው ምስጋናችን።

፪. ሰላም ለማርያም፡ ጽዮን እናታችን፤
ኪዳነ ምሕረት፡ ድንግል ንግሥታችን፤
ተዋሕዶ ሃይማኖት፡ ቤተ ክርስቲያናችን፤
ርስትሽ ነንና፡ በሕዝብነታችን፤
ይሰማ በአርያም፡ ይኸ መዝሙራችን።

፫. ለሰውነታችን፡ ለመንፈስ ምግባችን፤
ለሕመም መድኃኒት፡ ለደዌ ፈውሳችን፤
ከክፋት፥ ከኃጢአት፥ ከሞት መዳኛችን፤
በመከራ ጊዜ፡ ተስፋ መጽናኛችን፤
በምነትና ምግባር፡ የትግሥት ፍሬአችን።

፬. ለግል፥ ለቤተሰብ፥ ለኅብረት ኑሮአችን፤
ለአንድነት፥ ለፍቅር፥ ለሰላም ግባችን፤
ለሰብአዊ መብት፥ ለፍትሕ ዋስትናችን፤
አጥቂ እንዳይጎዳን፡ አለኝታ ጋሻችን፤
ለድል አድራጊነት፡ መሣሪያ ኃይላችን።

፭. ለዚህ ፊደላችን፡ ለግእዝ ቋንቋችን፤
ለእውቀት፥ ለጥበብ፥ ለሥልጣኔአችን፤
ለልማት፥ ለዕድገት፡ መሠረት ሕንፃችን፤
በተፈጥሮ ውበት፡ ገነት አገራችን፤
የምንኖርበት፡ የታሪክ ክብራችን።

፮. ለኖኅ ልጆች ውኅደት፡ የዘር ሓረጋችን፤
ለኢትዮጵያዊነት፡ መጠሪያ ስማችን፤
ለማንነታችን፡ ልዩ ማስረጃችን፤
በቀስተ ደመና፡ ነጻነት ልብሳችን፤
የማርያም መቀነት፡ ሰንደቅ ዓላማችን።

፯. አንበሳው ክርስቶስ፡ ምልክት አርማችን፤
ካምላክ ያገኘነው፡ ሕገ መንግሥታችን፤
ማንም የማይነጥቀን፡ የሰማይ ወርቃችን፤
የምንጠብቀው፡ ያደራ ውርሳችን፤
ቅዱሱ ኪዳን ነው፡ ሕያዉ ውርሳችን።

## የኢትዮጵያውያን፡

## <u>የመከራ ጊዜ መዝሙር።</u>

ኢትዮጵያ ሆይ፣ ሀገራችን!
        ረስቼሽ እንደኾን፡ ቀኜ ትርሳኝ፤
ያላሰብሁሽ እንደኾን፡
        መላሴ ትናጋዬን፡ ሰልቶ ይውጋኝ።
ከደስታዬ ኹሉ በላይ፡ ኢትዮጵያ ሆይ!
        አንቺ ባትኾኝ፡ ስደት ይብላኝ።
አቤቱ ፈጣሪያችን፡ በኢትዮጵያ ቀን፡
        ጠላቶቿን ኹሉ አስብ፤
አፍርሷት፡ ኢትዮጵያን፡
        እስከመሠረቷ ድረስ፡ የሚሉትንም ሕዝብ።
እናንት ትምክህተኞች፡ የኢትዮጵያ ጸሮች፣
        የተንኰላችሁን ብድራት፤
የሚመልስ ነው አምላካችን፡
        በፍትሕ በተአምራት፤
በሚጠሉሽ ላይ፡ በእውነት፣
        በቅን ለሚፈርደው ንጉሥ፡ ምስጋናችን ይብዛለት።
ኢትዮጵያ ሆይ፣ ሀገራችን!
        ረስቼሽ እንደኾን፡ ቀኜ ትርሳኝ።

## የኢትዮጵያውያን፡

## <u>የሰንደቅ ዓላማ መዝሙር።</u>

ኢትዮጵያ (ድንግል ማርያም) ሆይ! ደስ ይበልሽ፤
በአምላክሽ ኃይል በንጉሥሽ (በኢየሱስ ክርስቶስ)።
        ተባብረዋልና፡ (ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት)ልጆችሽ፤
        አይነካም ከቶ ነጻነትሽ።
ብርቱ ናችውና ተራሮችሽ፤
አትፈሪም ከጠላቶችሽ።
        የድል ሰንደቅ ዓላማችን፤
        ይኑርልን ለክብራችን።

+ + +

# THE SEVEN

# HOLY COVENANTS

According to the long and *living* Ethiopian Tradition, there are Seven Covenants, as enshrined in the Scriptures, that God made with humanity ever since Creation.

The first of these Covenants is signified and eternalized by the Matrimony of Adam and Eve (Gen. 2/21-25, Mt. 19/4-6); the second, by the Rainbow of Noah (Gen. 9/8-17); the third, by the Bread and Wine Offering of Melchizedek (Gen. 14/18-20); the fourth, by the Circumcision of Abraham (Gen. 17/1-14); the fifth, by the Ark of Moses (Deut. 5); the sixth, by the Throne of David (2Sam. 7/8-16); the seventh and the last, by the Crucified Body and Blood of Jesus Christ, born of the Virgin Mary (Mt. 26/26-29).

The Covenants, as described above and each symbolized by real signs, are personified by humble individuals who pleased God with their true love for Him. These persons became unique and parties of their respective Covenants with God following their singular triumphs over great trials of various physical and spiritual dimensions. And these trials were meant to test the truthfulness of their love for God before each one of them actually won His favor to be chosen as a representative party for the specific Divine Covenant.

These Seven Holy Covenants constitute ETHIOPIA or THE ETHIOPIAN. In other words, Ethiopia or the Ethiopian is these Seven Covenants, and these Seven Covenants are Ethiopia or the Ethiopian. Devoid of them, or outside the context and realm of these Seven Covenants, there is no Ethiopia nor the Ethiopian.

As a matter of fact, the Biblical Testimony or the Truth of the Old and the New Testaments endorses and identifies Ethiopia conclusively as the True Israel, and the Ethiopians as the True Israelites. Hence, the existence of Ethiopia and the life of the Ethiopian are both based on and intertwined by these Seven Covenants. Not only do the religious, the cultural and the social fabrics of the Ethiopians' lives, but also their educational, economic and political principles emanate from these Covenants. This is ETHIOPIANHOOD.

The above testimony is spelled out in the book entitled Ethiopia: The Classic Case in greater detail and summarized in the following Testimonials.

\+ + +

# THE ETHIOPIAN CREED

We Ethiopians believe in One God, God the Father, Almighty who possesses all, Maker of the Heavens and Earth, the visible and the invisible.

We believe in God the Son, Jesus Christ, One Lord, the only begotten Son of the Father, who was with Him before the creation of the world. He is Light from Light, True God from True God, begotten not made, and, in His Divine Essence, one with His Father. All things were made by Him, and without Him nothing whatsoever was made, in Heavens or on Earth.

He came down from Heavens for our sake, for the sake of humanity, for our salvation. He was Incarnate in the womb of the Virgin Mary by the Divine Work of the Holy Spirit, and, acquiring the human soul and the human flesh from Her, became the Perfect Man.

In the days of Pontius Pilate, He suffered, was crucified, died and was buried for our sake. And He rose from the dead on the third day, ascended in glory into Heaven and sat on His Throne at the right-hand of His Father.

He will come again in glory to judge the living and the dead. There is no end to His Kingdom.

We believe in God the Holy Spirit. He is the life-giving Spirit who proceeds from God the Father, spoke through the Prophets, and, by the atonement of Jesus Christ, descended upon the Apostles and filled the world with His Grace. We worship and glorify Him with the Father and the Son.

We believe in the One Church of The Holy Covenant that was founded by the Word of God, Jesus Christ, initially in the Hearts of the Patriarchs, and later sustained by His Divine Messages through the Prophets, and finally brought to perfection through the Holy Spirit by His convocation of the Apostles, and where His Body and Blood is offered as Sacrifice for the Holy Communion with God, and where the Sacramental Blessings of the Holy Spirit are bestowed upon and communicated to all believers.

We believe in One Baptism for the remission of sins.

We believe in the Resurrection from the dead and the Life to come, world without end. Amen.

# THE TESTIMONIAL
# OF THE ETHIOPIANS ON THE HOLY COVENANT

We Ethiopians believe in our Ethiopianhood of the Holy Covenant that embodied and conserved the Seven Divine Covenants the Lord granted to humanity.

Our God, in the Era of the Genesis, founded the Ethiopian Entity on the Covenant of the Soul, through the Matrimony of Adam and Eve.

Then in the Patriarchal period, He raised it, through Noah's Rainbow, Melchizedek's Offering and Abraham's Circumcision, to the next stage of its eschatological growth.

In the transitional Era of the Old Testament, He structured it, through Mose's Ark and David's Throne, to the finishing level that caused to bring about, under the Covenant of the Law, the genealogical union of the Ethiopian Queen Makkedda and the Israelite King Solomon.

Finally, in the Era of the Everlasting Life, He brought it to completion with the Sacrificial Body and Blood of His Son Jesus Christ, born of the Virgin Mary, who is the pure seed descended from that preordained genealogical union, thus culminating the Ethiopian Entity with the Eternal Crown of the Covenant of the Holy Spirit.

We believe that Ethiopia, as such, represents the Kingdom of God on Earth constituting the three Houses of the People, of the Administration and of the Priesthood achieved through such progressive development in Her uninterrupted existence under the protection and guidance of the Holy Covenant.

We believe that Jesus Christ who is the Son of God and in the name of whom we are called Christians and who is born of the seed that sprung from Shem, Ham and Japhet, in the Ethiopian image of nationhood, ordination and kingship of His precursor, Melchizedek, is our Eternal Priest and King.

We believe that the Mother of God, the Virgin Mary, who is the True Mother of the Living and the Eternal Ark of the Covenant, is the personification of Ethiopia, our Queen in Heavens and on Earth and in whose name we are called Ethiopians.

We believe that the tri-coloured banner of Green, Yellow and Red, symbolizing the sign of the Rainbow, is our Eternal National Flag entrusted to us by God through Noah.

We believe that the Divine Word of **"the Conquering Lion of the Tribe of Judah"** is ascribed to Jesus Christ who is the ultimate manifestation of the Holy Covenant, and the Prophetic Word of **"Ethiopia Stretches out Her Hands to God"** is attributed to the Virgin Mary, and that both Words of the Holy Spirit are our Eternal Divine Seal we received from Our God as a Nation of The Holy Covenant.

We believe that our spiritual birth from God, through the Grace of the Holy Baptism of The Covenant, entitled us to be heirs and servants of the Kingdom of God.

We believe that, in order for us to maintain such Divine birthright privilege, to confirm our inheritance of God's Kingdom and to continue rendering our pertinent services, it is our constant commitment to absolve our sins through incessant repentance and partake the Holy Communion of Our Lord Jesus Christ.

We believe that the genuine manifestation and the distinctive identification of our Faith in the Ethiopianhood of The Holy Covenant are best demonstrated by the typical Ethiopian deed that we perform in consideration and reflection of our love for both Jesus Christ and the Virgin Mary.

We believe that it is our God who, in accordance with His Word of The Covenant, inscribed in our hearts, taught us and made us to preserve in our lives this Ethiopianhood, which is the embodiment of the Holy Covenant. Amen.

## PRAYER OF THE ETHIOPIANS

## IN GLORIFICATION OF THE LORD

Our Father God! We thank You, and glorify You for the prayer which Your Son Jesus Christ taught us to say, **"Our Father who art in Heaven, Hallowed be Your Name. Your Kingdom come. Your Will be done on Earth as it is in Heaven. Give us this day our daily bread. And forgive us our debts, as we forgive our debtors. And do not lead us into temptation; but deliver us from the evil one. For, Yours is The Kingdom, and The Power, and The Glory, forever. Amen. "** and, through His atonement, for the answer You gave us to our supplication in that prayer.

You provided us with everything that pertains to our spiritual and material needs for the body as well as for the soul. Your generosity for us is bountiful; Your mercy, complete; Your love, perfect, and Your grace, overflowing.

Through the salvation of Your Son, born of the Holy Virgin Mary, the Grace of the Holy Spirit descended over and filled the whole world. Thus, today You reside not only in Heavens, but on Earth as well. Your Name is hallowed also on Earth. Your will that is done in Heavens is done also on Earth. Your Kingdom has come and is revealed on Earth.

By Your endowment of Nature, We recognized that You have arranged for our daily bread and for the entire life-long provisions of our bodily needs.

You gave us, on daily basis, the Holy Sacrament of the Body and Blood of Your Son as nourishment for our Soul, and as an assurance for our salvation and eternal life. Through the same Sacrament, You exonerated us completely from our sins and iniquities once for all, and empowered us to forgive the debts of our debtors.

For us to be Your Children, You granted us the exaltation of the spiritual birth of Baptism and the Sacrament of the Grace of Penance. You led us out of every temptation, delivered us from evil, and overthrew the powers of the Devil and Death that dominated our lives. Finally, You ordained for us the honour and the privilege to live in the Rapture of Your Resurrection.

O Lord! We are always grateful to You for Your inexpressible generosity, mercy, love and grace, as well as for all our needs that You provided us before we even ask You.

We wait for the time You promised us to come, when Your Kingdom of Truth, in which we are now blessed to live, under the Kingship of Jesus Christ, **"The Conquering Lion of the Tribe of Judah",** will prevail and destroy Evil, Sin and Death completely. Yes, we wait for the day when It actually reveals Itself to the material world and universally reigns over the whole realms of Creation.

Power, Glory and Kingdom are Yours, today as ever and forever, world without end. Amen.

## PRAYER OF THE ETHIOPIANS

## IN EXALTATION OF THE HOLY MOTHER.

Our Holy Mother Mary! With the Words of Greeting of the Angel Saint Gabriel, we bow to You in solemn salutation saying, “Hail, O Favoured One!” You are Virgin both in soul and in body. Because of Your perfect chastity, You became the Mother of the Almighty God. And so, You deserve such glorious salutation.

Your womb bore the Holy Adam who is the Sacred Fruit of the Tree of Life. Hence, You are the Holy Eve, the Chosen and the Blessed One among all the women.

In the early times, the Prophets spoke of You as **“Ethiopia stretches out Her Hands to God”,** and we addressed you as ‘Our Mother Zion’.

Rejoice, O Our Queen in Heavens and on Earth! God, through Your instrumentality fulfilled His promise of our Salvation and granted His Eternal Covenant of Mercy to His Creation. And so, we always praise You saying. “You are the Blessed, full of Grace.”

In the Words of Jesus Christ, our Saviour, Priest and King, we are Your children, committed to Your Maternal guardianship; and You are our Holy Mother, entrusted to our spiritual dedication. Thus, we believe Your Motherhood that has never forsaken Your beloved Son will always be with us.

We thank Our Gracious Father, God the Most High, for His Benevolence of such magnitude. World without end, Amen.

# ኢትዮጵያ፡
# የእግዚአብሔር መንግሥት አገልግሎት፡
# መመሪያ ሥርዓት፡፡

## መቅድም

እኛ ኢትዮጵያውያን፡ በሃይማኖትና በቃል ኪዳን ጸሎቶቻችን፥ እንዲሁም፡ ለሰማዩ አባታችን፡ ለልዑል እግዚአብሔርና ለዘለዓለማዊቷ እናታችን፡ ለቅድስት ድንግል ማርያም፡ በምናቀርባቸው የምስጋና ቃሎቻችን ውስጥ የተገለጹትን፡ የእምነት መመሪያዎቻችንን ተከትለን፡ ይኸው፡ የኢትዮጵያዊነት ሕይወታችንን በየግላችን እየኖርን እንገኛለን፡፡

ከዚህ የተነሣ፡ እግዚአብሔር፡ በቸርነቱ ብዛት፡ እያንዳንዳችን፡ በኢየሱስ ክርስቶስ በተገኘው ጸጋ፡ የዘለዓለማዊ ክብሩና የባሕርይ ገናንነቱ ተካፋዮች እንድንኾን ባደረገባት መንግሥቱ ውስጥ፡ መሰል የሌላትንና አምላካዊት የኾነችውን፡ የዜግነት መብት፡ በነፍስና በሥጋ፥ በመንፈስም አጎናጽፎናል፡፡ ይኸውም፡ ለኢየሱስ ክርስቶስ፡ ቀዳሚ አርአያና ለኢትዮጵያዊነት ደግሞ፡ መደበኛው ግንድ እንደኾነው፡ እንደመልከ ጼዴቅ ሰውነት ኹሉ፡ እኛም፡ በነፍስ ወከፍ፡ እየራሳችንን በንስሓ እያደስን፡ ቅዱሱን ቁርባን የምንቀበል በመኾናችን፡ የአንድነትና የሦስትነት ባሕርያት ላላቸው፡ ለሦስቱ የእግዚአብሔር መንግሥት ዘርፎች፡ ማለትም፡ ለቤተ ሕዝብ፥ ለቤተ ምልክናና ለቤተ ክህነት ባለቤነትነት የበቃንበት፡ ያ፡ በመንፈስ ቅዱስ የተቀዳጀነው፡ የእግዚአብሔር ልጆች የመኾን ክብር ነው፡፡

እንግዴህ፡ በኪዳነ ልቦና ተመሥርቶና በኪዳነ ኦሪት ጸንቶ፡ በኪዳነ መንፈስ ቅዱስ የተፈጸመውን፡ ይህን የመሰለውን መለኮታዊ በረከት ለመቀበል የታደልን፡ እኛ የኢትዮጵያ ልጆች፡ ይህንኑ፡ ከእግዚአብሔር ያገኘነውን ዘለዓለማዊ ጸጋ፡ በየግላችንና ለየግላችን ብቻ ሳይኾን፡ በኅብረትና ሌሎች ወገኖቻችንም፡ ለዚሁ የንስሓ ሕይወት እንዲበቁ በማድረግ፡ እውን በኾነ ሕያው አገልግሎት፡ በምግባር ተርጉመን፡ ለፍሬ ማብቃት እንደሚገባን ተገነዘብን፡፡ ደግሞም፡ ለግል፥ ለቤተሰብና ለኅብረት ኑሮአችን፡ መመሪያ እንዲኾነን፡ ከፈጣሪያችን የተሰጠን፡ ይህ አምላካዊ ሥርዓት፡ በተለይ፡ በእኛ በኢትዮጵያውያን ዘንድ፡ እስካሁን ጸንቶና ተጠብቆ የኖረ በመኾኑ፡ ወደፊትም፡ ከትውልድ ወደትውልድ እየተላለፈ የሚኖር እንጂ፡ በማንም ፍጡር ሊሻር የማይቻል፥ የማይገባም መኾኑን፡ በጠለቀ ሃይማኖታዊ መንፈስ ተረዳን፡፡

በዚህ መልክ፡ ከጥንት አባቶቻችንና እናቶቻችን ሲያያዝ መጥቶ፡ እነሆ ዛሬ እኛ የተረከብነውንና ኢትዮጵያዊ ግዳጃችን የኾነውን፡ ይህንኑ ተልእኳችንን፡ አጠናክረን ለመቀጠል እንችል ዘንድ፡ በዚሁ በያዝነው የእውነተኛ ኢትዮጵያዊነታችን አቋም፡ እስከመጨረሻው ጸንተን፥ በመንፈስ ቅዱስም፡ አንድ ልብ ኾነን፥ የእግዚአብሔርን ቃል፡ መሠረታችንና መመሪያችን፥ መነሻችንና መድረሻችን አድርገን፡ በቁርጥ በመነሣት፡ ተባብረን መሥራት እንዳለብን አምነን ተስማማን፡፡

## መግቢያ

ለዚህ ስምምነታችን፡ መሠረትና አዕማድ፥ መመሪያና ፋና ከኾኑን፡ የእግዚአብሔር ቃላት መካከል፡ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የተናገራቸው፡ ከዚህ የሚከተሉት ይገኛሉ፡፡ እነዚህም፡-

፩ኛ፡- ቀደም ብሎ፡ በመጀመሪያ፡ በብሉዩ ኪዳን፡ **"እኔ ራሴ፡ ሕጌን በልቡናቸው አኖራለሁ፤ በልባቸውም እጽፈዋለሁ፡፡ ስለዚህ፡ ሰው፡ ባልንጀራውን፡ 'እግዚአብሔርን እወቅ' ብሎ አያስተምርም፤ ኹሉ ያውቁኛልና!"**

፪ኛ፦ ኋላም፡ በመጨረሻ፡ በአዲሱ ኪዳን፡ "**ከእናንተ፡ ኹለቱ፡ በምድር ላይ፡ በሚለምኑት ነገር ኹሉ ቢስማሙ፡ በሰማያት ካለው ካባቴ ዘንድ ይደረግላቸዋል። ኹለት ወይም ሦስት፡ በስሜ በሚሰበሰቡበት፡ በዚያ በመካከላቸው እኾናለሁና!**" ሲል ያሰማቸውና በትንቢተ ኤርምያስ፡ ምዕራፍ ፴፩፥ ቁጥር ፴፩-፴፬፥ ቀጥሎም፡ በማቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ ፲፰፥ ቁጥር ፲፰-፳ ተጽፈው የሚነበቡት ናቸው።

እግዚአብሔር፡ እንዲህ አድርጎ፡ እርሱን እናውቀው ዘንድ፡ በየልቦናችን የጻፈውን ሕጉንና ያስተማረንን ትምህርቱን፥ በቃሉም ያሰማንን ተስፋውን አምነንና ተከትለን፡ በየግል ሰውነታችን ስንኖረው የቆየውን የአገልግሎት ሕይወታችንን፡ አሁን ደግሞ፡ እርሱ ራሱ፡ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስና ቅድስት እናቱ፡ ድንግል ማርያም፡ ዙፋናቸው፡ በመንፈስ ቅዱስ ተዘርግቶ፡ በሰብሳቢነታቸውና በመሪነታቸው ተቀምጠው በሚያካኺዱት፡ በዚህ የመንፈስ ቅዱስ አገልግሎታችን አማካይነት፡ በጋራ እንዲቀጥል እናደርግ ዘንድ፡ መለኮታዊ ጥሪው እነሆ ቀረበልን።

እኛም፡ ጥሪውን ተቀብለን፡ ቀደም ብሎ፡ በየልቦናችን ተቀርጾና ከዚህ በታች በፊደላት ገዝፎ በተጻፈው መመሪያ መሠረት፡ በግል፡ ከእያንዳንዳችን፥ በጋራ ደግሞ፡ ከኹላችን የሚጠበቀውን፡ የኢትዮጵያዊነት ተግባር ለመፈጸም፡ ተዘጋጅተን እንገኛለን። ይህንንም፡ በመለኮታዊቷ መንግሥት ዙፋን ፊት፡ በእውነትና በመንፈስ ቆመን፡ ለዚህ ያበቃንን ጌታ፥ ቅድስት እናቱንም በማመስገንና እንደገና የምስክርነት ቃላችንን በይፋ በመስጠት እናረጋግጣለን።

## አንቀጽ አንድ

### ስያሜ

የአገልግሎቱ ስም፡ "ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት አገልግሎት" ነው። በዚህ መመሪያ ውስጥ፡ ባጭር ቃል፡ "አገልግሎት" ተብሎ ይጠቀሳል። እያንዳንዱም ቅርንጫፍ፡ በሚገኝበት አድራሻ የሚታወቅ ይኾናል።

## አንቀጽ ኹለት

### አቋም

የአገልግሎቱ አቋም፡ ከዚህ በኋላ፡ "ቀኖናዊ መርህ" ወይም "ሃይማኖታዊ መመሪያ" እየተባለ በሚጠቀሰው፡ በኢትዮጵያ የቅዱሱ ኪዳን ተዋሕዶ ሃይማኖት ላይ የተመሠረተ ነው። የአገልግሎቱ መመሪያዎች፥ ምግባሮችና ሥርዓቶች ኹሉ፡ ያላንዳች መዛባት፡ በሙሉ የሚመነጩት፡ ከዚህ ቀኖናዊ መርህ ብቻ ይኾናል።

ይህ ቀኖናዊ መርህ፡ በኢትዮጵያውያን ልቦና ተመዝግበውና በልማድ ታውቀው፥ በቃል ሲነገሩና በምግባር ሲፈጸሙ በኖሩት፥ ዛሬ ግን፡ ከላይ፡ በዚህ ዕትም ውስጥ፡ በጽሑፍ ሠፍረውና የዚህ መመሪያ አካል ኾነው፡ ከነመዘሙሮቻቸው በሚነበቡት፦

፩ኛ፦ የኢትዮጵያውያን ሃይማኖት፥

፪ኛ፦ የኢትዮጵያውያን ቃል ኪዳን፥

፫ኛ፦ ኢትዮጵያውያን፡ ለእግዚአብሔር የሚያቀርቡት ምስጋና፥

፬ኛ፦ ኢትዮጵያውያን፡ ለድንግል ማርያም የሚያቀርቡት ሰላምታ በተባሉት ቃላት ተብራርቷል።

የእነዚህ አራት ጸሎታት ትርጓሜና ሐተታ፡ በዚህ መመሪያ ውስጥ አባሪ ኾነው ከተያያዙት፡ የኢትዮጵያውያን መዝሙሮች ጋር፥ በተለይ፡ "ኢትዮጵያዊው፥ በማንነቱ ፍለጋ!"፥ "ኢትዮጵያ፡ የዓለሙ መፋረጃ!"፥ "Ethiopia: The Classic Case"፥ እንዲሁም፡ "ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊነት" በተባሉት፡ በንቡረ እድ ኤርምያስ ከበደ ወልደ ኢየሱስ ተዘጋጅተው በታተሙት መጻሕፍት፡ በሰፊውና በሚበቃ ተተንትኖ ተሰጥቷል፡፡ እነዚህ መጻሕፍት፡ በአገልግሎቱ አባሎች እጅ ኾነው፡ የማስታወሻ ግልጋሎታቸውን፡ ለዘወትር ማበርከታቸውን ይቀጥላሉ፡፡

# አንቀጽ ሦስት

## ዓላማ

የአገልግሎቱ ዓላማ፡ በዚህ መመሪያ ውስጥ፡ ባጭር ቃል፡ "ሕያው ውርስ" ተብሎ የሚጠራውንና በአንቀጽ ኹለት፡ "ቀኖናዊ መርህ"፥ ወይም "ሃይማኖታዊ መመሪያ" የተባለውን፡ ቅዱሱን ኪዳን፡ ፩ኛ፡- እያንዳንዱ አባል፡ በሃይማኖታዊነቱም ኾነ በምግባራዊነቱ፡ ራሱ ሕይወት አድርጎት መኖሩን፡ በሚያስተማምን ኹኔታ ማረጋገጥ፤

፪ኛ፡- ራሱን በንስሓ አድሶ ለሚቀርብ፡ "ኢትዮጵያዊ ነኝ" ለሚለው፡ ወንድ ኾነ ሴት ለኾነ ወገንና ለዚህ ኢትዮጵያዊነት ሊበቃ በሚፈቅድ፡ በማናቸውም ግለሰብ ሕያው ሰውነት፡ ይኸው ቅዱሱ ኪዳን፡ በተቻለ መጠን፡ በግል፡ በእያንዳንዱ አባል፥ በጋራ ደግሞ፡ በአገልግሎቱ አማካይነት፡ ተገቢ በኾነው ዘዴና መንገድ፡ በጤናማነት እንዲጠበቅ፥ በዚሁ የትንሣኤ ባሕርዩም እንዲቀጥል፥ በፍጥረተ ዓለሙ ዘንድ እንዲታወቅና በዘለዓለማዊ ህልውናው፡ ለትውልደ ትውልድ እንዲተላለፍ ማድረግ ነው፡፡

# አንቀጽ አራት

## የዓላማው ጊዜያዊ አፈጻጸም

የአገልግሎቱ ዓላማ፡ በግል በእያንዳንዱ አባል፥ በጋራም በአገልግሎቱ ቤተ ሕዝብና የእርሱ ዘርፎች በኾኑት፡ በቤተ ክህነቱና በቤተ ምልክናው አማካይነት፡ ከዚህ በታች በተዘረዘሩት ምግባራት፡ በጊዜያዊ መልኩ፡ በሥራ ላይ ውሎ ይፈጸማል፡፡-

፩ኛ፡- እያንዳንዱን ኢትዮጵያዊ፥ በአጠቃላይም፡ "ኢትዮጵያዊ ነኝ!" የሚለውን ወገንና ሌላውን ግለሰብ፡-

(ሀ) በግንባር ተገናኝቶ በማነጋገር፥

(ለ) በቃልና በጽሑፍ በማስተማር፥

(ሐ) ድርሰቶችን አሳትሞ በማሠራጨት፥

(መ) በነፋስ ድምፅና በነፋስ ሥዕል፥ በኅዋ መልእክትና በደብዳቤ አማካይነት በማስተላለፍ፥

(ሠ) በንግግርና በሥዕል ጥብጣብ ቀርጾ በማዳረስ፥

(ረ) ስብሰባን፥ ጉባዔንና የጥናት ሸንጎን በማዘጋጀት፥

(ሰ) "ኪዳናችን" በተባለው የአገልግሎቱ ጦማረ ሕዝብና በሌላ በማናቸውም የመገናኛ ዘዴ በመጠቀም፡ ሕያዉን ውርስ በሚመለከትና ራስን በንስሓ፡ እንዴት ለእውነተኛው ኢትዮጵያዊነት ማብቃት እንደሚቻል፡ ሙሉ እውቀትንና መረጃን፥ መመሪያንና የምክር እርዳታን እንዲያገኙ ማድረግ፤

፪ኛ:- ከዚህ መመሪያ ሥርዓት ጋር በተያያዘው: "ቃለ ዓዋዲ" በተባለው: የኢትዮጵያ: የነጋሪት ቀላጤ: ስለሰበካ ጉባዔ አስተዳደር: በጥቅምት ፲፫ ቀን፥ ፲፱፻፷፫ ዓ.ም. ታትሞ በወጣው ደንብ መሠረት ተቋቁመው: ኢትዮጵያውያን ካህናትን ለሚያስተዳድሩና ምእመናንን ለሚያገለግሉ ሰበካ ጉባዔዎች፥ እንዲሁም: የሰበካ ጉባዔዎች ባልተቋቋሙባቸው ሥፍራዎች ለሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና ሌሎች ወገኖች ጭምር: ከኢትዮጵያ ቤተ ሕዝብ ሠርፀው: የአገልግሎቱ ዘርፎች በኾኑት: በቤተ ክህነቱና በቤተ ምልክናው አማካይነት: ዓቅም የሚፈቅደውን: ማናቸውንም አስፈላጊና ተገቢ የኾነ: መንፈሳዊና ሥጋዊ አገልግሎትንና እርዳታን ማበርከት፤

፫ኛ:- ሕያዉን ውርስ: ከትውልድ ወደትውልድ እና ከአንዱ ወደሌላው ለማስተላለፍ፥ በበለጠም ለማሳወቅ: እስካሁን በመሣሪያነት ያበረከቱት አገልግሎት ይቀጥል ዘንድ: ኢትዮጵያውያን መምህራንን፥ ካህናትን፥ መተርጉማንን፥ ደራስያንን፥ ሠዓልያንንና ከሕያዉ ውርሳችን ጋር የተዛመደ ሙያና ጥበብ ያላቸውን ግለሰቦች ኹሉ ፈልጎ ማግኘት፥ ለአገልግሎት መመደብ እና/ወይም ማሠልጠን፤

፬ኛ:- ኢትዮጵያውያን ሕፃናትና ትልልቆች ጭምር: የማንነታቸው መገለጫ የኾነው: የቅዱሱ ኪዳን ሕዝብነታቸው: ለመቼውም ጊዜ: በአእምሮአቸውና በየልቦናቸው ተቀርጾ ይኖር ዘንድ: ከሕያዉ ውርስ የሠረፁትንና የኢትዮጵያ ብቸኛ ሀብቶች የኾኑትን የእውቀትና የሙያ፥ የሥነ ምግባርና የባህል ቅርሶች የያዘውን ሥርዓተ ትምህርት ተከትለው የሚያስተምሩ የትምህርት ተቅዋማትን: አግባብ በኾኑ ቦታዎች መመሥረት፤

፭ኛ:- ለኢትዮጵያውያንና ለሌሎችም: የሥራ ዕድልን በመፍጠር: የአገሪቱ ምድር በምታፈራቸው ሰብሎችና ንጥረ ነገሮች: እየተሠሩ የሚወጡትን የምርት ውጤቶች: በዓይነትና በመጠን ከፍ ለማድረግ ይቻል ዘንድ: ከሕያዉ ውርስ ባህል ጋር የሚስማሙትን ልዩ ልዩ ያገርቤት ዕንስ አሳቦችንና ጥበቦችን፥ የሥነ እውቀትና የተግባረ እድ ሙያዎችን: አግባብ ባለው መንገድና ዘዴ አጥንቶ መለየት፥ ማዳበርና በሥራ ላይ ማዋል፤

፮ኛ:- ሕያዉን ውርስ በሚመለከት: የጥናት፥ የምርምር እና/ወይም የትርጉም ሥራ በማካኼድ: የአገልግሎቱ ዓላማዎች: በተግባር ላይ ውለው: ሙሉ ተፈጻሚነትን እንዲያገኙ የሚያደርግ: አንድ አጠቃላይ የኾነ የመካነ አእምሮ ድርጅት ማቋቋም፤

፯ኛ:- ለዓላማዎቹ መሳካት: ተጻራሪ አቋም ከሌላቸው ሌሎች ግለሰቦች፥ ማኅበሮችና ድርጅቶች ጋር መተባበር::

# አንቀጽ አምስት

## አባልነት

### ንዑስ አንቀጽ ፩
### አባልነት

በአገልግሎቱ ውስጥ ሙሉ አባል ለመኾን: ማናቸውም ግለሰብ: ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ይዘቶች አሟልቶና ፈጽሞ እንዲገኝ ያስፈልጋል::

፩ኛ: የኢትዮጵያዊነቱ መታወቂያ በኾነው: በቀኖናዊው መርህ ውስጥ በተብራራው: በኢትዮጵያ የቅዱሱ ኪዳን ተዋሕዶ ሃይማኖት ጸንቶ የሚገኝ፥

፪ኛ: "ኢትዮጵያዊ ነኝ" ብሎ: ራሱን በንስሓ አድሶና በቅዱስ ቁርባን አጽድቆ የሚቀርብ፥

፫ኛ: ቀኖናዊዉን መርህ: በእውነትና በታማኝነት መቀበሉን፥ ይህንኑም ጠብቆ፥ አጽንቶና አሳውቆ የሚኖር መኾኑን: የቃል ኪዳን ምስክርነትን በይፋ በመስጠት የሚያረጋግጥ፥

፬ኛ፡ ቀኖናዊው መርህ የሚጠይቀውን የኑሮ ሥርዓት ተከትሎ፡ ራሱን፡ የዚያ ሥርዓት ሕያው መገለጫ በማድረግ፡ ሕይወቱን የሚመራ፥

፭ኛ፡ ቀኖናዊው መርህ በደነገጋቸው ሥርዓቶች መሠረት፡ በቤተሰቡ ውስጥ ከሚተዳደረው፡ ከእያንዳንዱ አባል ጀምሮ፡ ተገቢውን መመሪያና ትምህርት በመስጠት፡ የኢትዮጵያዊን ማንነትና የኢትዮጵያዊነትን ምንነት፡ ከትውልድ ወደትውልድ ለማስተላለፍ ያለበትን ተግባርና ኃላፊነት ተገንዝቦ፡ ይህንኑ ግዳጁን በሥራ ላይ የሚያውል፥

፮ኛ፡ የአገልግሎቱን ዓላማዎችና በዚህ መምሪያ የተደነገጉትን ሥርዓቶች፡ ራሱ አክብሮ የሚፈጽምና በቆራጥነት የሚያስፈጽም፥

፯ኛ፡ ዕድሜው፡ አሥራ ስምንት ዓመታት፡ ወይም ከዚያ በላይ የኾነ ሰው፡ ጾታና ሙያ፥ የመኖሪያ ቦታም ሳይወስነው፡ በአገልግሎቱ የሥራ ዘርፎች ውስጥ የሚመደቡትን አገልጋዮች ለመምረጥ እና/ወይም፡ ራሱ ለመመረጥ የሚያበቃውን የሙሉ አባልነት መብትን ማግኘት ይችላል።

ነገር ግን፡ ማናቸውም አባል፡ በዚህ መመሪያ ሥርዓት ውስጥ፡ በየአንቀጹ ለተጠቀሱት፡ ለአገልግሎቱ ሙሴነት፥ እንዲሁም፡ ለሦስቱ የአገልግሎት ቤቶች፡ ማለትም፡ ለቤተ ሕዝቡ፥ ለቤተ ክህነቱና ለቤተ ምልክናው ሊቀ መንበርነት ለሚያበቃው ምርጫ እጩ መኾን የሚችለው፡ ሰላሣ ዓመታት፡ ወይም ከዚያ በላይ ከኾነ የዕድሜ ደረጃ የደረሰ መኾኑ ሲረጋገጥ ብቻ ይኾናል።

## ንዑስ አንቀጽ ፪
## የአባልነት ሥርዓት

አንድ ሰው፡ አባል ለመኾን፡ በቅድሚያ፡ ቢያንስ ቢያንስ፡ ኹለት ነባር አባሎች፡ በቃል ወይም በጽሑፍ፡ ለአገልግሎቱ ሙሴ በሚያቀርቡት ማስታወሻ፡ እጩ ኾኖ መቅረብ ይኖርበታል፤ ይህንኑ፡ ሙሴው ደግፎ፡ ወደአገልግሎቱ ምርፋቅ ካስተላለፈው በኋላ፡ በዚያ ምርፋቅ ስብሰባ ላይ የተገኙት አባሎች፡ እጩውን በአንድ ድምፅ ተስማምተው፡ ሲቀበሉት፡ አባል ይኾናል። ይህም ውሳኔ፡ ለመላው አባሎች በይፋ ይገለጣል።

## ንዑስ አንቀጽ ፫
## ከአባልነት ስለመገለልና ስለመታገድ

ማናቸውም አባል፡ የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነቱን ካልካደ፥ ወይም በራሱ ፍላጎትና ጥያቄ ካልኾነ በስተቀር፡ ከአባልነቱ አይገለልም፤ አይታገድም።

አንድ አባል፡ ኾነ ብሎ፡ በአገልግሎቱ መመሪያ ውስጥ የሠፈሩትን ሥርዓቶች፡ በተደጋጋሚ ቢተላለፍ፡ ወይም የአገልግሎቱን መልካም ስምና በጎ ዓላማ የሚጻረር ጠባይ ቢያሳይ፡ ወይም ይኸው ግለሰብ፡ ከአባልነቱ፡ የመገለል ወይም የመለየት ጥያቄና ፍላጎት ኖሮት፡ ይህንኑ፡ በቃል ወይም በጽሑፍ ገልጾ፡ ለሙሴው ማስታወሻ ቢያቀርብ፡ ሙሴው፡ ይህንኑ ጉዳይ፡ ወዲያው፡ ለምርፋቁ፡ በመጀመሪያው ስብሰባ ላይ ያቀርበዋል።

በዚህ ኹኔታ የሚገኘውን አባል፡ ሙሴውና በእርሱ የተመረጡ አባሎች፡ እስከሦስት ጊዜያት ድረስ፡ በሽምግልና መልክ ይጠይቁታል፤ ያነጋግሩታል፤ ይመክሩታል። ነገር ግን፡ ይኸው አባል፡ የቀረበለትን ጥያቄና ምክር የማይቀበል ኾኖ በሚገኝበት ጊዜ፡ በራሱ ፍላጎትና ፈቃድ፡ ከአባልነቱ እንደታገደ፡ ወይም ጨርሶ እንደተወገደ ይቆጠራል።

ይኹን እንጂ፡ አንድ አባል፡ በዚህ መልክ፡ ከአባልነቱ መገለሉ፡ ወይም መታገዱ፡ ወይም ጨርሶ መወገዱ የሚረጋገጠው፡ ጉዳዩ፡ በመጀመሪያ ደረጃ፡ ከመላው የምርፋቁ አባሎች መካከል፥ ቀጥሎም፡ በመጨረሻው ደረጃ በሚደረገው፡ በሚቀጥለው የአገልግሎቱ ጠቅላላ ጉባዔ ላይ፡ ከመላው አባሎች መካከል፡ እጅግ ቢያንስ፡ ኹለት ሦስተኛዎቹ በተገኙበት ቀርቦ ሲወሰን ብቻ ነው።

ይህም: ፩ኛ: በማቴዎስ ወንጌል: ምዕ. ፲፰÷ ቁ. ፲፩-፳ የተጻፈውን: የጌታን ቃል በማብራራት÷ ፪ኛ: በመጀመሪያውም ኾነ በኹለተኛው ደረጃ: በጉዳዩ ላይ: የመጨረሻ ውሳኔ ከመሰጠቱ: አሥራ አምስት ቀኖች በፊት: የስብሰባውን ጊዜና ቦታ በማመልከት: ለተጠያቂነት ያበቃውን ምክንያት የያዘው መግለጫ: በቃል ወይም በጽሑፍ: ለሚመለከተው አባል ከደረሰው በኋላ ይኾናል::

ይህን ጉዳይ: ከመልካም ፍጻሜ ለማድረስ ሲባል: የአባሎች ልዩ ስብሰባ እንዲደረግ የሚያስፈልግ ኾኖ ቢገኝ: ይህን የመሰለው አሠራር: አገልግሎቱ ለቆመለት ዓላማ: ተገቢነት ያለው በመኾኑ: ማናቸውም የሚመለከተው ወገን: ስብሰባው እንዲጠራ: በቀጥታ: ለሙሴው ማሳሰብ÷ ሙሴውም: ከምርፋቁ ጋር ተመካክሮ: ጉባዔውን ሊሰበስብ ይችላል::

በዚህ መልክ: ከአባልነት የተለየው ግለሰብ: በማናቸውም ጊዜ: በንስሓ ቢመለስ: የነበረበትን የአባልነት ክብር የመቀዳጀት መብቱ: ምንጊዜም የተጠበቀለት መኾኑ: ከአባልነቱ: በራሱ ፈቃድ በሚለይበት እና/ወይም በአገልግሎቱ ጠቅላላ ጉባዔ ውሳኔ መሠረት በሚወገድበት ዕለት: በገሃድ ይነገረዋል::

# አንቀጽ ስድስት

## ስብሰባዎች

አገልግሎቱ: ዓላማቸው አንድ የኾነ÷ ነገር ግን ይዘታቸው የተለያየ: የስብሰባ ሥርዓቶች አሉት:: እነዚህም: ከዚህ የሚከተሉት ናቸው:-

### ንዑስ አንቀጽ ፩
### ሰሙናዊ ስብሰባ

በዚህ ሰሙናዊ ስብሰባ: አባሎች ኹሉ: በየሳምንቱ እሑድ: በዕለተ ሰንበተ ክርስቲያን: ከንጋቱ ፲፪ ሰዓት በፊት: ከመላው ቤተሰባቸው ጋር: በቅድስት ቤተ ክርስቲያን ተገኝተውና የቅዳሴ ሥርዓተ ጸሎታቸውን ፈጽመው: ቅዱስ ቁርባንን ይቀበላሉ::

ይህም: ኢየሱስ ክርስቶስና እናቱ ድንግል ማርያም: በመንበራቸው ተቀምጠው: የቃል ኪዳን ልጆቻቸው የኾኑት ኢትዮጵያውያን: ሴቶቹም÷ ወንዶቹም: በቅዱሱ ገበታ ዙርያ: በፊታቸው ተሰባስበው: ቅዱስ ሥጋውንና ክቡር ደሙን የሚቀበሉበት: አማናዊው የእግዚአብሔር መንግሥት ጉባዔ ነው:: በዚህ ቅዱስ ጉባዔ: ሌሎቹ የአገልግሎቱ ስብሰባዎች ኹሉ ይቀደሳሉ፤ መሠረታቸውና ቀዳሚያቸውም ስለኾነ: ይህ ሰሙናዊ ስብሰባ: በአባሎች ዘንድ: በፍጹም ልዕልና ይከበራል::

ከቅዳሴው ሥርዓት በኋላ: በቤተ ክርስቲያን የተገኙት አባሎች: ከኢትዮጵያዊነት የዘር አባታቸው: ከመልከ ጼዴቅ: በቃል ኪዳን የወረሱትን: የተቀደሰውን የጠበል ጠዲቅ ሥርዓታቸውን ያከናውናሉ:: ቀጥሎ: የትምህርት ውይይታቸውን ያካኺዳሉ:: በመጨረሻ: የእርስ በርስ ንግግር ተለዋውጠው: የተወሰነው ጊዜያቸው ሲያበቃ: በፍቅር ተሰነባብተው ይለያያሉ::

### ንዑስ አንቀጽ ፪
### ወርኃዊ ስብሰባ

የየወሩ አሥራ ስድስተኛ ቀን: ማለት የኪዳነ ምሕረት በዓል: ከሳምንቱ ሰኞ እስከረቡዕ ሲውል: በወዲህኛው የዕለተ እሑድ: ሰንበተ ክርስቲያን÷ ከኀሙስ እስከቅዳሜ ሲውል ደግሞ: በሚቀጥለው የዕለተ እሑድ ሰንበተ ክርስቲያን: ሥርዓተ ቅዳሴያቸው ከተፈጸመ በኋላ: ከጧቱ ፬ እስከ ፯ ሰዓት ድረስ: የአባሎች ወርኃዊ ስብሰባ ይደረጋል::

የዚህ ስብሰባ ዓላማ፡ አባሎች፡ ከነቤተሰቦቻቸው፡ በበለጠ ተቀራርበው፡ ማኅበራዊ ግንኙነታቸውን እንዲያጎለምሱ፥ በመካከላቸው ያለውን የኅብረተሰብ አንድነት እንዲያጠናክሩ፥ ለአባሎችና አባሎች ላልኾኑ ጭምር ለሚያስፈልገው በጎ ምግባር፡ የእርስበርስና የኅብረት መረዳዳትን እንዲያጎለብቱ፥ እንዲሁም፡ እያንዳንዳቸው፡ በነፍስ ወከፍ፥ በአጠቃላይ ደግሞ፡ ኹሉም፡ አገልግሎቱ ለተቋቋመበት ዓላማ፡ ያላቸውን ግንዛቤ እንዲያሳድጉ፡ ማድረግ ይኾናል።

በእነዚህ ስብሰባዎች ላይ፡ ንግግሮችና ውይይቶች፥ ባህላዊና ትምህርታዊ መዝናኛዎች፡ እንዲሁም ሌሎች ማኅበራዊ ዝግጅቶችና የአዳዲስ አባሎች ትውውቅ፥ ደግሞም፡ የአገልግሎቱን ተግባሮች በሚመለከት፡ የማስታወቂያዎችና የመግለጫዎች ሥርጭት እንደአስፈላጊነታቸው ሊቀርቡ ይቻላል።

**ንዑስ አንቀጽ ፫**

**የጠቅላላው ጉባዔ፡ ዓመታዊ ስብሰባ**

በየዓመቱ መጨረሻ ቀዳሚት ሰንበት እና በተከታይዋ ሰንበተ ክርስቲያን እሑድ፡ መላው አባሎች የሚገኙበት፡ የአገልግሎቱ ዓመታዊ ስብሰባ ይደረጋል።

የዚህ ስብሰባ ዋና ዓላማዎች፦

፩ኛ፡ ቤተ ምልክናውንና ቤተ ክህነቱን የሚያስገኘውን፡ የቤተ ሕዝቡን ጠቅላላ ጉባዔ ተወካዮች፡ በየሦስት ዓመታቱ ለመምረጥ፥

፪ኛ፡ ሙሴው፡ አገልግሎቱ ስለሚገኝበት ኹኔታ፡ የሚያቀርበውን ጠቅላላ መግለጫ ለመስማት፥

፫ኛ፡ መላው አባሎች ሊያውቋቸው፡ ወይም ለእነርሱ ሊቀርቡ የሚገቡ ሌሎች ጉዳዮች ካሉ፡ እነዚያን ለመስማት፡ ወይም በእነዚያ ላይ ውሳኔ ለመስጠት ይኾናል።

ለጠቅላላው ጉባዔ የሚመረጡት ተወካዮች፡ ቁጥራቸው፡ እንደአባሎቹ ብዛት እየታየ ይወሰናል። ነገር ግን፡ ምንጊዜም፡ ከመላው አባሎች ቁጥር፡ ከአራት አንድ እጅ አያንስም።

**ንዑስ አንቀጽ ፬**

**ልዩ ስብሰባ**

ሙሴው ወይም ምርፋቁ፡ አስፈላጊ መስሎ በታየው፡ በማናቸውም ጊዜ፡ የአባሎች ልዩ ስብሰባ፡ ወይም የአገልግሎቱ ጠቅላላ ጉባዔ እንዲደረግ መጥራት ይችላል። ደግሞ፡ ከአባሎቹ መካከል፡ አንድ ሦስተኛው ያህል፡ በቃል ወይም በጽሑፍ የጠየቁ እንደኾነ፡ ሙሴው፡ ከምርፋቁ ጋር ተወያይቶ፡ ልዩው ስብሰባ እንዲደረግ ይጠራል።

ማናቸውም ልዩ ስብሰባ እንዲደረግ የሚተላለፈው ጥሪ፡ ለዓመታዊው ስብሰባ ጥሪ በሚፈጸመው መልክ ይኾናል። "ለስብሰባው ቀርቦ ይታያል" ተብሎ፡ በቃል ከተነገረው፡ ወይም በጥሪው ማስታወቂያ ውስጥ ከተጠቀሰው በቀር፡ አባሎቹ በሚያደርጉት በማናቸውም ልዩ ስብሰባ ላይ፡ አንዳችም ሌላ የሥራ ጉዳይ ቀርቦ አይታይም።

**ንዑስ አንቀጽ ፭**

**ምልዓተ ጉባዔ**

በአገልግሎቱ የሥራ ጉዳይ ላይ ተነጋግሮ ለመወሰን፡ የኃላፊነትና የተጠያቂነት ሥልጣን ያለውን ምልዓተ ጉባዔ ለማግኘት፡ ምንጊዜም፡ ድምፅ የመስጠት መብት ያላቸው አባሎች፡ አብዛኛዎቹ በአካል የሚሳተፉበት ስብሰባ እንዲኖር ያስፈልጋል።

በዚህ ጊዜ፡ በአገልግሎቱ ጠቅላላ ጉባዔና በምርፋቁ፥ እንዲሁም፡ ለተለያዩ ጉዳዮች ተመርጠው በሚደረጉ፡ የየሕዋሳቱ ስብሰባዎች ላይ፡ ሙሴው ወይም የየስብሰባው ሊቀ መንበርና አብዛኛዎቹ የጉባዔው፡ ወይም የምርፋቁ፡ ወይም የየሕዋሱ አባሎች ከተገኙ፡ ምልዓተ ጉባዔ እንዳለ ተቆጥሮ፡ የአገልግሎቱን ሥራ ለማካኼድ ይቻላል።

ሙሴው በማይገኝበት ጊዜ፡ ግልገል ሙሴው፥ ወይም፡ የየቤቱ ሊቀ መንበርና የየሕዋሱ ሰብሳቢ በማይገኝበት ጊዜ ደግሞ፡ ምክትሉ፡ ስብሰባዎችን፡ በሊቀ መንበርነት ይመራል። ምልዓተ ጉባዔ በማይገኝበት ጊዜ፡ ቁጥራቸው አናሳ የኾነው አባሎች፡ ስብሰባውን፡ ከአሥር ቀኖች ላሽበለጠ፡ ለሌላ ዕለት ቀጥረው መለያየት ይችላሉ።

ምልዓተ ጉባዔ መኖሩ ከተረጋገጠ በኋላ፡ ለየስብሰባው የቀረበው ጉዳይ ወይም ምርጫ፡ በተባበረ አንድ ድምፅ እንዲወሰን፡ የተቻለው ይደረጋል። ይህ ያልተቻለ እንደኾነ፡ ጉዳዩ ወይም ምርጫው፡ ለዕጣ ይቀርባል። የዕጣ አወጣጡ ሥርዓት፡ በሓዋርያት ሥራ፡ ምዕ. ፩፥ ቁጥር ፲፭-፳፮ ላይ በተጻፈው መሠረት፡ ተገቢው ጸሎት ተከናውኖ ይፈጸማል።

## ንዑስ አንቀጽ ፮
## የስብሰባ ጥሪና በስብሰባ አለመገኘት

የስብሰባ ጥሪ፡ ቀንና ሰዓት፥ ቦታውና ምክንያቱ ጭምር፡ ለመላው አባሎች፡ በሙሴው፡ ወይም በግልገል ሙሴው አማካይነት፡ በመጨረሻው ሰሙናዊ ወይም ወርኃዊ ስብሰባ ላይ፡ በቃል ይነገራል። የስብሰባ ጥሪ፡ በቃል ወይም በጽሑፍ ሊኾን ይችላል። በጽሑፍ እንዲኾን ያስፈለገ እንደኾን፡ ጥሪው፡ ከላይ የተጠቀሱትን ዝርዝሮች ከያዘ መግለጫ ጋር፡ ለስብሰባው ከተወሰነው ቀን በፊት፡ ቢያንስ፡ ከአምስት፥ ቢበዛም፡ ከሃያ ቀኖች ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ፡ ለእያንዳንዱ አባል እንዲደርሰው ይላካል።

በስብሰባ ላይ ተገኝቶ ድምፅ የመስጠት መብት ያለው፡ አንድ አባል፡ በተጠራበት ስብሰባ ላይ የመገኘት ኃላፊነት አለበት። ምናልባት፡ በስብሰባው ላይ ለመገኘት የማይችልበት ምክንያት ቢያጋጥመው፡ ይህንኑ፡ በቅድሚያ፡ ለሙሴው ወይም ለሚመለከተው ሰብሳቢ ማስታወቅ ይኖርበታል።

ማናቸውም አባል፡ በስብሰባው ላይ ያልተገኘበትን ምክንያት በመግለጽ፡ ለሙሴው ወይም ለሚመለከተው ሰብሳቢ፡ መልእክት ሳይልክ፡ በሦስት ተከታታይ ስብሰባዎች ላይ ሳይገኝ ቢቀር፡ ሙሴው፡ ለዚያ የአገልግሎት ወንበር፡ ሌላ አባል፡ በጊዜያዊነት ተክቶ፡ በመምሪያው መሠረት ተገቢው እንዲፈጸም ያደርጋል።

## ንዑስ አንቀጽ ፯
## የስብሰባ ሥራ፡ ቅደም ተከተል

የአገልግሎቱ ጠቅላላ ጉባዔና የመደበኛ ሸንጎዎች፥ የምርፋቁና የሌሎቹ ሕዋሳት ስብሰባዎች ኹሉ፡ ተግባራቸውን የሚያካኼዱበት ቅደም ተከተል እንደሚከተለው ይኾናል፦

፩ኛ፡ ስብሰባውን በጸሎት መክፈት፤
፪ኛ፡ የስብሰባው ጥሪ ለተሳታፊዎቹ መድረሱን ማረጋገጥ፤
፫ኛ፡ አባሎች መገኘታቸውን፡ ስማቸውን በመጥራት ማወቅ፤
፬ኛ፡ ቃለ ጉባዔን ማንበብ፤
፭ኛ፡ መልእክቶችን መቀበል፤
፮ኛ፡ አገልጋዮችን መሠየምና የአባልነትን ጥያቄ መመርመር፤
፯ኛ፡ የዋና አገልጋዮችን የሥራ ፍሬዎች፡ መስማት፤
፰ኛ፡ የየሕዋሳቱን የሥራ ውጤቶች ማዳመጥ፤

፱ኛ፡ ውዝፍ የሥራ ጉዳዮችን ማጠናቀቅ፤
፲ኛ፡ አዳዲስ የሥራ ጉዳዮችን መመልከት፤
፲፩ኛ፡ ማስታወቂያዎችን መንገር፤
፲፪ኛ፡ ስብሰባውን በጸሎት መዝጋት።

ይህ የሥራ ቅደም ተከተል፡ በማናቸውም ስብሰባ ላይ በተገኙት አባሎች፡ ስምምነት ሊሻሻል የሚቻል ሲኾን፡ ማናቸውም የሥራ ጉዳይ፡ በቅድሚያ እንዲታይ የመወሰኑ ሥልጣን ግን፡ የስብሰባው ሊቀ መንበር ብቻ ይኾናል።

# አንቀጽ ሰባት

## የአገልግሎት አቋም

አገልግሎቱ፡ ዓላማዎቹ ከግብ የሚደርሱበትን ተግባሮቹን ለማከናወን፡ የእግዚአብሔር መንግሥት የኾነችውን፡ የኢትዮጵያን አቋም ተከትሎ፡ ከዚህ በሚከተለው መልክ፡ ሥራዎቹን ያካኺዳል፤ ይፈጽማል።

## ንዑስ አንቀጽ ፩
## የጠቅላላው ጉባዔ አንድነትና የአገልግሎት ቤቶች ሦስትነት

በአገልግሎቱ ዓመታዊ ስብሰባ ላይ፡ በመላው አባሎች የሚመረጠው፡ የአገልግሎቱ ጠቅላላ ጉባዔ፡ ቤተ ሕዝቡን፥ ቤተ ምልክናውንና ቤተ ክህነቱን አዋህዶ የያዘው፡ አንድ ዓቢይ አካል ነው። አገልግሎቱ፡ ለጠቅላላው ጉባዔ፡ የአቋም ግንድ በኾነው፡ በቤተ ሕዝቡ፥ እንዲሁም፡ ከእርሱ በሚሠርፁት፡ በቤተ ምልክናውና በቤተ ክህነቱ አማካይነት፡ የአገልግሎቱን አውታር፡ በአጠቃላይና በየዘርፉ ዘርግቶ፡ ተግባሩን ያካኺዳል፤ ይፈጽማል።

## ንዑስ አንቀጽ ፪
## የሦስቱ የአገልግሎት ቤቶች፡ የተዋሕዶ ምሥጢር

የእግዚአብሔር መንግሥት ክፍሎች የኾኑት፡ እነዚህ በተዋሕዶ የጸኑት፡ ሦስት ቤቶች፡ እንደሥሉስ ቅዱስና እንደሰው አካል፡ የአንድነትና የሦስትነት ምሥጢር ያላቸው፡ አንድም፥ ሦስትም ኾነው፡ በኢትዮጵያዊው ሰውነትና በአንዲቱ ኢትዮጵያ ይሠራሉ። ይህም ማለት፡ አንዱ እግዚአብሔር አምላክ፡ በአብ፥ በወልድ፥ በመንፈስ ቅዱስ፡ እንዲህ፡ በሦስት ስም፥ በሦስት አካልና በሦስት ግብር ታውቆ፥ ተገልጦና መልቶ እንደሚሠራ፥ ደግሞም፡ አንዱ ሰብአዊ ፍጡር፡ ነፍስ፥ ሥጋና መንፈስ በተባሉ፡ በሦስት ስሞች፥ በሦስት አካላትና በሦስት ግብሮች ተጠርቶ፥ ገዝፎና ረቅቆ እንደሚኖር ኹሉ፡ እንዲሁ፡ እያንዳንዳቸው፡ የእግዚአብሔር መንግሥት የኾኑት ኢትዮጵያውያን ባስገኙት፡ በዚህ አገልግሎት፡ ቤተ ሕዝቡ፡ እንደአብ ወይም እንደነፍስ አካል፥ ቤተ ምልክናው፡ እንደወልድ ወይም እንደሥጋ አካል፥ ቤተ ክህነቱ፡ እንደመንፈስ ቅዱስ ወይም እንደመንፈስ አካል ኾነው ተግባራቸውን ያካኺዳሉ።

## ንዑስ አንቀጽ ፫
## የሦስቱ የአገልግሎት ቤቶች የሥራ ድርሻ

ከላይ፡ በንዑስ አንቀጽ ፪ የተገለጸውን ምሥጢር መሠረት በማድረግ፡ ቤተ ሕዝቡ፡ በውስጥ፡ የአባሎቹን፥ በውጭ ደግሞ፡ የሕዝቡን ጠቅላላ ፍላጎትና ግዳጅ፥ ቤተ ምልክናውም፡ በውስጥ፡ የአባሎቹን፥ በውጭ ደግሞ፡ የኅብረተሰቡን ሥጋዊ ፍላጎትና ግዳጅ፥ ቤተ ክህነቱም፡ በውስጥ፡ የአባሎቹን፥ በውጭ ደግሞ፡ የምዕመናኑን መንፈሳዊ ፍላጎትና ግዳጅ ለማሟላትና ለመፈጸም የሚያስችለውን፡ ተገቢውን ተግባርና አገልግሎት፡ በየበኩላቸው ያከናውናሉ።

# አንቀጽ ስምንት

## የአገልጋዮች ምርጫና ሢመት

መላውን አገልግሎት፥ ጠቅላላውን ጉባዔ፥ ሦስቱን የአገልግሎት ቤቶችና ምርፋቁን፥ ሌሎቹንም የአገልግሎቱን ሸንጎዎችና ስብሰባዎች፡ በመንፈስ ቅዱስ የሚሰበስቡትና የሚመሩት፡ ራሳቸው፡ ኢየሱስ ክርስቶስና ድንግል ማርያም የመኾናቸውን ሃይማኖታዊ ምሥጢር፡ በእውነትና በመንፈስ፡ አውቀውና ተረድተው፡ ኃላፊነታቸውን በፍጹም ፈቃደኛነት በመቀበል፡ የአገልግሎቱን ዓላማዎች፡ በተግባር ላይ የሚያውሉለትን አገልጋዮች፡ አገልግሎቱ፡ ከዚህ በሚከተለው ሥርዓት መርጦ፡ በየመንበራቸው ይመድባል።

## ንዑስ አንቀጽ ፩
## የአገልግሎት ሥዩማንና አባሎች አመራረጥ

### ሀ. ሙሴ

የኢየሱስ ክርስቶስና የእናቱ ድንግል ማርያም፡ ተቀዳሚ ተጠሪ ኾኖ፡ አገልግሎቱን፡ በባለአደራነትና በበላይነት የሚሰበስበውና የሚመራው፥ የሚያስተዳድረውና የሚቆጣጠረው፥ ሌላውንም የአገልግሎት ኀላፊነቱንና ተግባሩን የሚፈጽመው ዋና አገልጋይ፡ ሙሴ ተብሎ ይሠየማል። የሙሴው ምርጫ፡ መላው አባሎቹ በተገኙበት፡ በጠቅላላው ጉባዔ ይፈጸማል። ያንንም ስብሰባ፡ በሊቀ መንበርነት እንዲመራ፡ የጠቅላላው ጉባዔ አባሎች፡ ከመካከላቸው፡ በዕድሜ አረጋዊነት እና/ወይም በአባልነት ተራ፡ ቅድሚያ ያለውን አባል፡ ሰብሳቢ ይኾን ዘንድ፡ በአንድ ድምፅ ይወስናሉ። የእርሱ፡ ለዚህ ጊዜያዊ ኃላፊነት መመደብ፡ ለሙሴነት ምርጫ፡ እጩ ከመኾን አይከለክለውም።

### ለ. ሊቃነ መናብርት

ከሙሴው ቀጥለው ረዳቶች ተጠሪዎች በመኾን፡ አገልግሎቱን በቀንደኛነት የሚያገለግሉት፡ የቤተ ሕዝቡ፥ የቤተ ክህነቱና የቤተ ምልክናው ሊቃነ መናብርት፡ ከቤተ ሕዝቡ ጠቅላላ ጉባዔ ተወካዮች መካከል፡ በሙሴው አቅራቢነትና ሊቀ መንበርነት፡ በጠቅላላው ጉባዔ ይመረጣሉ።

የእነርሱም ሢመት፡ በጠቅላላው ጉባዔ ከጸደቀ በኋላ፡ እያንዳንዳቸው፡ ምክትሎቻቸውን፥ እንዲሁም፡ የቤተ ምልክናውና የቤተ ክህነቱ ሊቃነ መናብርት፡ በአገልግሎት የሚረዷቸውን ሹማምንት፡ ከጠቅላላው ጉባዔ ሕዝባውያን፥ ካህናትና ምሉካን ተወካዮች መካከል መርጠው፡ ለሙሴው ያቀርባሉ። እርሱ፡ ምርጫቸውን፡ ሲቀበለው፡ አባሎቹ፡ የተመደበላቸውን የኃላፊነት ሥራ ይጀምራሉ።

በዚህ የአገልግሎት ጥሪና ድልድል ውስጥ የሌሉት፡ የቀሩት የጠቅላላው ጉባዔ ተወካዮች፡ የቤተ ሕዝቡ መደበኞች ባልደረቦች ኾነው፡ የሕግ አውጭነት ተግባራቸውን ያካኺዳሉ።

የቤተ ሕዝቡ ሊቀ መንበር፡ በዚህ ኃላፊነቱ ምክንያት፡ ምንጊዜም፡ የግልገል ሙሴነቱን የአገልግሎት ቦታ የሚይዝ እርሱ ይኾናል።

ሦስቱም ሊቃነ መናብርት፡ በየሊቀ መንበርነት ኀላፊነታቸው፡ የምርፋቁ አባሎች ናቸው።

### ንዑስ አንቀጽ ፪
### የአገልግሎት ሹማምንት ብቅዓትና የሥራ ዘመን

ከላይ በንዑስ አንቀጽ ፩ የተጠቀሱት ባለአደራ አገልጋዮች፡ እያንዳንዳቸው ለሚይዙት የኃላፊነት መንበር በሚያበቋቸው፡ በሦስቱም የኢትዮጵያዊነት የሥልጣን ጸጋዎችና ሙያዎች፡ ማለትም፡ በሕዝባዊነት፥ በክህነትና በምሉክነት የተሟሉ ኾነው መገኘታቸውን፥ እነርሱም፡ የአገልግሎቱን ኃላፊነት፡ በፍጹም ፈቃደኝነት ለመቀበል መዘጋጀታቸውን፡ ጠቅላላው ጉባዔ፡ በጊዜው ኃላፊዎች አማካይነት፡ በቅድሚያ ያረጋግጣል።

የእነዚህ አገልጋዮች፡ የሥራ ዘመን፡ ሦስት ዓመታት ይኾናል። ይህ የአገልግሎት ዘመን በሚያበቃበት ጊዜ፡ ኹሉም፡ ወይም ጥቂቶቹ፡ ወይም አንዳቸው፡ አገልግሎታቸውን ሊቀጥሉ የማይችሉበት በቂ ምክንያት ካልተገኘ፡ ወይም በየራሳቸው ፈቃድ ሥራቸውን መልቀቅ ካልፈለጉ በስተቀር፡ ቦታቸውን እንደያዙ፡ የተለመደ አገልግሎታቸውን ይቀጥላሉ።

### ንዑስ አንቀጽ ፫
### የተለቀቁ የአገልግሎት ወንበሮች

በሙሴው መንበር፥ እንዲሁም፡ በቤተ ሕዝቡ፥ በቤተ ክህነቱና በቤተ ምልክናው፥ በምርፋቁና በሌሎቹም የአገልግሎቱ ሕዋሳት ውስጥ፡ በሞት፥ በሥራ መልቀቅ ወይም በሌላ ምክንያት፡ የማናቸውም የአገልግሎት አባል ወንበር የተለቀቀ እንደኾነ፡ በሙሴው፡ ግልገል ሙሴው ይተካል፤ በሌሎቹ ቦታዎች ግን፡ ሙሴው፡ ያለመዘግየት፡ ጊዜያዊዉን ተተኪ ይመድብበታል።

ይህም የሚኾነው፡ ምርፋቁ፡ በመደበኛ ስብሰባው፡ ወይም ለዚሁ ጉዳይ ብሎ በሚያደርገው ልዩ ስብሰባ ተነጋግሮ፡ የጊዜያዊዉን አገልጋይ ተተኪነት እስኪያጸድቀው፡ ወይም ተገቢ የኾነ ሌላ አገልጋይ እስኪተካበት ድረስ ነው። በዚህ መልክ የተሠየመው አባል፡ ምርጫው፡ በጠቅላላው ጉባዔ እስከሚጸድቅበት፡ እስከሚቀጥለው ዓመታዊ ስብሰባ፡ ወይም፡ በአንቀጽ ስድስት፥ ንዑስ አንቀጽ ፬ መሠረት፡ ልዩ ስብሰባ ተደርጎ፡ ተተኪው ሰው እስኪመረጥ ድረስ፡ ወንበሩን ይዞ ሲያገለግል ይቆያል።

## አንቀጽ ዘጠኝ

### የምርጫ ሱባኤ

ምርጫዎች ኹሉ የሚካኼዱት፡ መላው አባሎች፡ የመንፈስ ቅዱስ መሪነት፥ ረድዔትና በረከት እንዳይለያቸው፡ ቀደም ብለው የሚያደርጉት፡ የሱባዔ ሥርዓት ካበቃ በኋላ ይኾናል። ይኸውም፡ እያንዳንዱ የአገልግሎቱ ምርጫ፡ በዚህ መልክ በሚከናወንበት ጊዜ፡ ምርጫው፡ በመንፈስ ቅዱስ እንደተፈጸመ ታምኖበት፡ ለተመራጩ ወይም ለተመራጮቹ፡ "ሥዩመ እግዚአብሔር" የሚለውን የጸጋ ማዕርግ የሚያጎናጽፍ በመኾኑ ነው።

## አንቀጽ አሥር

### የዓላማው ቋሚ አፈጻጸምና የሥራ አመራር

በአጠቃላይና በዝርዝር፡ ሥጋዊና መንፈሳዊ የኾነው የአገልግሎቱ ተግባር የሚከናወነው፡ ከላይ በአንቀጽ ሰባት የተመለከተውን፡ የአገልግሎት አቋም በመከተል፡ ቀጥሎ በተብራራው መሠረት፡ የአገልግሎቱ ሙሴ፡ በተጠሪነት በሚመራው፡ ጠቅላላ ጉባዔ፥ እንዲሁም፡ በቤተ ሕዝቡ፥ በቤተ ምልክናውና በቤተ ክህነቱ አማካይነት ይኾናል።

## ንዑስ አንቀጽ ፩
## የሙሴው መንበር

በሙሴው የአገልግሎት ኃላፊነት ሊፈጸሙ ከሚገባቸው ተግባሮች መካከል፡ ከዚህ የሚከተሉት ይገኛሉ።

፩ኛ፡ በመላው አባሎችና እንዲሁም፡ ቤተ ምልክናውንና ቤተ ክህነቱን በሚያዋህደው፡ በቤተ ሕዝቡ ጠቅላላ ጉባዔ ስም፡ አገልግሎቱን ወክሎ፡ ማናቸውንም የአገልግሎቱን ጉዳይ ይፈጽማል፤

፪ኛ፡ የአገልግሎቱን ጠቅላላ ጉባዔና ምርፋቁን፥ መላው አባሎች የሚገኙባቸውንም ሌሎች ስብሰባዎች ይሰበስባል፤ ይመራል፤

፫ኛ፡ ዋናው የአገልግሎቱ ሥራ ፈጻሚ እንደመኾኑ መጠን፡ በአገልግሎቱ ጠቅላላ ጉባዔ የጸደቁት የአስተዳደርና የሥራ ጉዳዮች፥ መርሓ ግብሮችና ዕቅዶች፡ በተግባር ላይ እንዲውሉ ያደርጋል፤

፬ኛ፡ ስላለፈውና ስለመጪው፡ የአገልግሎቱ ዓመታዊ የሥራ ፍሬና ዕቅድ፥ ደግሞም፡ ስለዓመታዊው የገቢና የወጪ ኹኔታና ድልድል የሚዘጋጁት መግለጫዎች፡ ከጠቅላላው ጉባዔ በፊት፡ ለምርፋቁ ይቀርቡ ዘንድ፡ በጊዜው መጠናቀቃቸውን ይከታተላል፤

፭ኛ፡ የአገልግሎቱ የአስተዳደርና የሥራ ኹኔታ፥ የሒሳብና የንብረት ይዞታም፡ በምን ደረጃ ላይ እንደሚገኝ፡ ቢያንስ ቢያንስ፡ በዓመት አንድ ጊዜ፡ በአገልግሎቱ ተቆጣጣሪዎች እንዲመረመር አድርጎ፡ ውጤቱ፡ ለአገልግሎቱ ጠቅላላ ጉባዔ መቅረቡን ያረጋግጣል፤

፮ኛ፡ የአገልግሎቱ ስብሰባ ሊደረግ በማይችልበት ጊዜ፡ በአገልግሎቱ ስም፡ አግባብ ያለውን ማናቸውንም ተግባር ይፈጽማል፤ ነገር ግን፡ ያን፡ የፈጸመውን ተግባር፡ ይጸድቅ ዘንድ፡ ለሚቀጥለው ጠቅላላ ጉባዔ ወይም፡ ለዚያው ጉዳይ ተብሎ ለሚጠራው ልዩ ስብሰባ ያቀርበዋል፤

፯ኛ፡ የአገልግሎቱን ብልጽግናና ደኅንነት ለማሳደግ፥ አስፈላጊነቱንና ጠቃሚነቱንም ከፍ ለማድረግ፡ በእርሱ ግምት ይረዳሉ የሚላቸውን ጉዳዮች፡ ተመርምረው ውሳኔ እንዲሰጥባቸው፡ ከሦስቱ ቤቶች አግባብ ላለው ለእያንዳንዱ፡ በምርፋቁ አማካይነት ያስተላልፋል።

## ንዑስ አንቀጽ ፪
## ቤተ ሕዝብና ጠቅላላው ጉባዔ

ቤተ ሕዝብ የሚባለው፡ ቤተ ምልክናውንና ቤተ ክህነቱን አጠቃልሎ የያዘውና እነዚህን ኹለት ዓበይት የአገልግሎት ቅርንጫፎች የሚያስገኘው ግንድ ነው። የአገልግሎቱ ዋና የአካል ክፍል ስለኾነ፡ ቤተ ሕዝቡ፡ በሙሴው ሰብሳቢነት፡ በዚህ መልኩ ሲሰበሰብ፡ ጠቅላላ ጉባዔ ይባላል። የዘወትር ስብሰባው ግን፡ በሊቀ መንበሩ ይካኼዳል።

ቤተ ሕዝቡ፡ የሕግ አውጪነትን ሥልጣን የያዘው የአገልግሎቱ ዓቢይ ዓምድ ስለኾነ፦

፩ኛ፡ ሥጋዊዉንም ኾነ መንፈሳዊዉን በሚመለከት፡ በውስጡ ከሚገኙት ንዑሳን ጉባዔዎች፥ እንዲሁም፡ ከቤተ ክህነቱና ከቤተ ምልክናው እየተጠኑ የሚቀርቡለትን ሥርዓቶችና ደንቦች፥ መምሪያዎችና የተግባር አሳቦች እየመረመረ ይወስናል፤

፪ኛ፡ የአገልግሎቱ ዓላማዎች በተግባር ላይ የሚውሉበትን፥ የአባሎቹ ሥጋዊና መንፈሳዊ ፍላጎቶች፡ በአጠቃላይ የሚሟሉበትንና ሌሎቹንም፡ በቤተ ሕዝብ ኃላፊነቱ፡ ሊፈጽማቸው የሚገቡትን፡ የዘወትር ግዳጆቹን እያከናወነ መምሪያዎችን ይሰጣል፤

፫ኛ፡ በእርሱ፡ ማለትም፡ በቤተ ሕዝቡ የተወሰኑት ጉዳዮች፥ የወጡት መምሪያዎችና የጸደቁት ተግባሮች፡ በሥራ ላይ እንዲውሉ፡ ሥጋውያን የኾኑትን፡ ወደቤተ ምልክናው፥ መንፈሳውያን የኾኑትን ደግሞ፡ ወደቤተ ክህነቱ ያስተላልፋል፤

፬ኛ፡ እነዚህንና የመሳሰሉትን ተግባሮቹን ለመፈጸም፡ በቤቱ ሊቀ መንበር መሪነት፡ በማናቸውም ጊዜ እየተሰበሰበ ሥራውን ያካኼዳል፤

፭ኛ፡ በተለይ ከዚህ የሚከተሉትን ተግባሮች ለመፈጸም፡ ከአገልግሎቱ ዓመታዊ ስብሰባ ቀደም ብሎ፡ በሙሴው፡ ወይም፡ ሙሴውን ለመምረጥ ከኾነ፡ ጉባዔው በሚሠይመው አባል ሰብሳቢነት፡ መደበኛ ጠቅላላ ጉባዔውን ያደርጋል።

ሀ. በየሦስት ዓመቱ፡ የአገልግሎቱን ሙሴ ለመምረጥ፥

ለ. በየሦስት ዓመቱ፡ በሙሴው ታጭተው የሚቀርቡትን፡ የቤተ ሕዝቡን፥ የቤተ ምልክናውንና የቤተ ክህነቱን ሊቃነ መናብርት፥ እንዲሁም የአገልግሎት ተቆጣጣሪውን ሢመት፥ በየዓመቱ ደግሞ፡ የምርጫ አስፈጻሚዎችን ምርጫ ለማጽደቅ፥

ሐ. ከሦስቱ የአገልግሎት ቤቶች ሊቃነ መናብርት ከሚቀርቡት፡ ዓመታዊ የሥራ ፍሬዎችና ከመጪው ዓመት ዕቅዶች የተጠናቀረውን የሙሴውን አጠቃላይ መግለጫ አዳምጦ፡ ተገቢውን መምሪያ ለመስጠት፥

መ. በጠቅላላው፡ በቤተ ክህነቱም ኾነ በቤተ ምልክናው ዘርፍ የተካኼደውና የተከናወነው፡ የአገልግሎቱ የሥራና የአስተዳደር፥ የሒሳብና የሀብት አያያዝ ውጤት እንዴት እንደኾነ፡ ከአገልግሎቱ ተቆጣጣሪ የሚቀርበውን አስተያየት ተቀብሎ፡ አስፈላጊውን ለመወሰን፥

ሠ. በእነዚህና በሌሎች ከፍተኛ የአገልግሎቱ ጉዳዮች ላይ ተነጋግሮ፡ ከጉባዔው የሚጠበቀውን ለማድረግ።

ቤተ ሕዝቡ፡ በውስጡ፡ ሥጋዊና መንፈሳዊ ተብለው በኹለት ወገን ተመድበው፡ የሃይማኖትና የአስተዳደር ጉዳዮችን በሚመለከት፡ ሕጎችንና ደንቦችን፥ ሥርዓቶችንና መመሪያዎችን እያጠኑና እያዘጋጁ፥ እንዲሁም፡ በዚህ ረገድ፡ ከቤተ ክህነቱና ከቤተ ምልክናው የሚተላለፉለትን ረቂቅ አሳቦች እየመረመሩ፡ ለውሳኔ የሚያቀርቡለት፡ ኹለት ንዑሳን ጉባዔዎች ይኖሩታል።

## ንዑስ አንቀጽ ፫
## ቤተ ክህነት

ቤተ ክህነቱ፡ የአገልግሎቱን የሕግ ተርጓሚነት ሥልጣን የያዘ ከመኾኑ ጋር፡ ከዚህ የሚከተሉት ተግባሮች ይኖሩታል፦

፩ኛ፡ ሃይማኖታዊ የኾኑትን እውነቶች መጠበቅና ማስጠበቅ፥

፪ኛ፡ የሥነ ምግባር አኗኗርና ሥርዓት እንዲከበሩ ማድረግ፥

፫ኛ፡ ክህነታዊ የኾኑትን አገልግሎቶች በሚገባ መስጠት፥

፬ኛ፡ በትምህርት የሚተላለፉትን እውቀቶች ማበርከት፥

፭ኛ፡ በተቃወሱ የእምነትና ሕግነክ ጥያቄዎች ላይ መበየን፥

፮ኛ፡ ረቂቃን የኾኑትን የሕይወትና የህልውና ነገሮች ማጥናት፥

፯ኛ፡ በጠቅላላና በዝርዝር፡ መንፈሳውያን ጉዳዮችን መመልከት።

በዚህ መሠረት፡ ቤተ ክህነቱ፦

ሀ. የቅዱሱ ኪዳን ተዋሕዶ ሃይማኖትና ምግባር፡ ከወንዶቹና ከሴቶቹ ሕፃናት ጀምሮ፡ እስከጐልማሶችና አረጋውያን ኢትዮጵያውያን ዘንድ ድረስ፡ በጥልቀትና በጥራት እንዲታወቅ፥ እንዲጠበቅም ያደርጋል፤

ለ. ኢትዮጵያዊነት፡ ከነቃል ኪዳናቱ ምሥጢርና ዜና መዋዕሉ ጋር፥ እንዲሁም፡ ግእዝን ከመሰሉት ሕያዋን ቅርሶቹ፥ ትውፊቶቹና ባህሎቹ ጋር፡ ምን እንደኾነ በትክክል ያስተምራል፤ ያስጠብቃልም፤

ሐ. በእግዚአብሔር መንግሥት ሥር፡ የኢትዮጵያዊ፡ የግልና የጋብቻ፥ የቤተሰብና የማኅበረሰብ የአኗኗር ሥርዓት፡ እንዴት እንደኾነ ያሳውቃል፤ ያስፈጽማልም፤

መ. የክህነት አገልግሎት፡ በተሟላና በተገባ መልክ መሰጠቱን ያረጋግጣል፤

ሠ. ሥጋዊዉንና መንፈሳዊዉን ትምህርት፡ ለዘመኑ ተገቢና አስፈላጊ በኾነ ሥርዓት ያካኺዳል፤ ለዚህ የሚኾነውን ሥርዓተ ትምህርት፥ መማሪያ መጻሕፍትንና ማስተማሪያ መሣሪያዎችን ያሰናዳል፤

ረ. ለክህነትና ለምልክና ተልእኮ፥ በጠቅላላም፡ ሕዝባዊ ለኾነው፡ ለማናቸውም ዓይነት የአገልግሎት ሥራ የሚያስፈልጉትን ሠራተኞችና ባለሙያዎች፥ መምህራንና ምሁራን ያሠለጥናል፤ ያዘጋጃልም፤

ሰ. በአገልግሎቱ ውስጥ፡ ሥጋዊዉና መንፈሳዊው ፍትሕ ርትዕ እንዲጠበቁ ያደርጋል፤ ፍርድንና ዳኝነትን የሚመለከተውን ሥራ ያካኺዳል፤ አከራካሪና አወዛጋቢ የኾኑ የሕግ ጉዳዮች ሲነሡ፡ መፍትሔውን ይሰጣል፤ የተዛባውንም ያስተካክላል።

## ንዑስ አንቀጽ ፬
## ቤተ ምልክና

ቤተ ምልክናው፡ የአገልግሎቱን የሕግ ፈጻሚነት ሥልጣን የያዘ ነው። ስለዚህ፡ ከራሱና ከቤተ ክህነቱ መንጭተው፡ በቤተ ሕዝቡ ጠቅላላ ጉባኤ የጸደቁትና የተወሰኑት ጉዳዮች ኹሉ፡ እንዲፈጸሙ የማድረግ ኃላፊነት አለበት።

በዚህ መሠረት፡ የአገልግሎቱ ዓላማዎች፡ በተግባር ላይ ውለው፡ ውጤት ይኖራቸው ዘንድ፡ ቤተ ምልክናው፡-

፩ኛ፡ በአጠቃላይና በዝርዝር፡ ለቤተ ሕዝቡ፥ ለቤተ ክህነቱና ለራሱም፡ ለቤተ ምልክናው፡ የሚያስፈልጉት ሥጋዊ ዝግጅቶችና ድርጅቶች ኹሉ እንዲሟሉ በማድረግ፡ የአገልግሎቱን ጠቅላላ የአስተዳደር አመራር፥ የጽሕፈት ሥራና የሒሳብ አያያዝ፥ የሀብት ልማትና የንብረት ጥበቃ፡ በኃላፊነት ይዞ፡ ተገቢ የኾነ ተግባሩን ያካኺዳል፤ በዚህ ኃላፊነቱ፡ የአባሎቹ ዝክረ ነገር፡ ከየክርስትና ስማቸው ዝርዝር ጋር፡ በመዝገብ መያዙን ያረጋግጣል፤

፪ኛ፡ በቤተ ክህነቱ እየተማሩና እየሠለጠኑ፡ ለአገልግሎቱ ሥራ የሚቀርቡትን ሕዝባውያን ሠራተኞች፥ ምሁራን ካህናትና ምሉካን ባለሙያዎች፡ መመሪያውን ሥርዓት በመከተል፡ እንዳስፈላጊነቱ፡ ከሙሴው እና/ወይም ከየቤቱ ሊቃነ መናብርት ጋር እየተመካከረ፡ በየተወሰነላቸው ቦታ ይደለድላል፤ ይመድባል፤ ያዛውራል፤ ዕድገት ይሰጣል፤ ለበለጠ ሥልጠና ወደቤተ ክህነቱ ይልካል፤ ያሰናብታል፤

፫ኛ፡ ከላይ በ፪ኛው ተራ ቁጥር ለተጠቀሱት አገልጋዮችና ሠራተኞች፡ ለየሥራቸው የሚያስፈልጋቸውን፡ አላቂና ኗሪ፥ ተንቀሳቃሽና ቋሚ መሣሪያ፥ እንዲሁም፡ ለግልና ለቤተሰብ ኑሮአቸው የሚኾናቸውን ቤትና ዕቃ፥ የዕለት ጉርስና የዓመት ልብስ ያቀርባል፤

፬ኛ፡ መላውን አባልና ሌላውንም ሕዝብ፡ በመብልና በመጠጥ፥ በልብስና በመኖርያ፥ በጤንነትና በሥራ ባለሙያነት፡ ራሳቸውን በማስቻል፡ መንፈሳዊ ሕይወታቸውንና ሥጋዊ ኑሮአቸውን ያሟላል፤

፭ኛ፡ የመላው አባልና የውጭውም ወገን ሥጋዊና መንፈሳዊ ደህንነት፥ ሰላምና ፀጥታ፡ በአስተማማኝ ኹኔታ የተጠበቀ መኾኑን ያረጋግጣል።

፮ኛ፡ ከላይ በተራ ቁጥሮች ከ፩ እስከ፭ የተዘረዘሩትን ተግባሮች ለማከናወንና ለእነዚሁ ተግባሮች ማካኼጃ የሚኾኑትን መሥሪያ ቤቶችና ድርጅቶች ለማቋቋም፥ እንዲሁም፡ ሌሎቹን የአገልግሎቱን ጠቅላላ ግዳጆች ለመፈጸም፡ በቂ የኾነ ሀብት ስለሚያስፈልግ፡ ይህን ወጪ ለመሸፈን፡ ገቢ የሚገኝበትን፥ የተገኘውና ያለውም፡ የሚጠበቅበትንና የሚለማበትን መልካም ዘዴ እያጠና ለፍሬ ያበቃል፤

፯ኛ፡ የአገልግሎቱን ዓላማዎች በመከተል፡ ሥጋዊዉን ወገን የሚመለከተውን፡ ማናቸውንም ተግባር ይፈጽማል።

## ንዑስ አንቀጽ ፩
## ምርፋቅ

ሙሴው፡ አገልግሎቱን የሚያበረክትበትና የኃላፊነት ተግባሩን የሚፈጽምበት፥ በእርሱ ሰብሳቢነት የሚካኼድ፡ አንድ ከፍተኛ ሕዋስ ይኖራል፤ እርሱም፡ ምርፋቅ ይባላል።

ይህ ምርፋቅ፡ የሦስቱ የአገልግሎት ቤቶች ሊቃነ መናብርት፥ እንዲሁም፡ ሙሴው የሚመርጣቸው፡ እያንዳንዱን ቤት፡ በእኩል መጠን የሚወክሉ፡ ቁጥራቸው፡ ከሦስት የማያንስ፡ ወይም ከዘጠኝ የማይበልጥ አባሎች፡ በባልደረብነት የሚገኙበት ነው።

ቤተ ሕዝቡ፥ ቤተ ምልክናውና ቤተ ክህነቱ፡ እያንዳንዳቸው በየዘርፋቸው የሚፈጽሙት ተግባርና አገልግሎት ሳይቋረጥ የሚካኼድ ኾኖ፡ በተለይ፡ ምርፋቁ፡ ከዚህ የሚከተሉት ኃላፊነቶች ይኖሩታል፦

፩ኛ፡ በቤተ ሕዝቡ፥ በቤተ ምልክናውና በቤተ ክህነቱ በኩል ያለውን የሥራ እንቅስቃሴና የአገልግሎት ውጤት መገምገም፥ እንዲሁም፡ የአማካሪው ሕዋስና የሌሎቹ ተጠሪ ሕዋሳት ሰብሳቢዎች የሚያቀርቧቸውን መግለጫዎች አዳምጦ፡ በእነዚህና በሌሎች የሥራ ጉዳዮች ላይ ተነጋግሮ፡ እንደነገሩ ኹኔታ፡ መምሪያ መስጠት፤

፪ኛ፡ ያለፈውንና የመጪውን፡ ዓመታዊ የሥራ ፍሬና ዕቅድ፥ እንዲሁም፡ የገቢና ወጪ ኹኔታና ድልድል በሚመለከት፡ ለጠቅላላው ጉባዔ ይቀርብ ዘንድ፡ ከሦስቱም ቤቶች ተዘጋጅቶ የተጠናቀረውን፡ የመጨረሻ መግለጫ መርምሮ ማጽደቅ፤

፫ኛ፡ የአባሎችንና ለኢትዮጵያዊነት እንዲበቁ የሚደከምላቸውን ወገኖች፡ ሥጋዊና መንፈሳዊ፥ እንዲሁም ማኅበራዊ ደኅንነት፡ በበለጠ ለማሳደግ፡ "ተገቢነትና ተስማሚነት አላቸው" ብሎ የሚገምታቸውን ተግባራት፡ በቤተ ክህነቱ ወይም በቤተ ምልክናው በኩል እንዲጠኑ እያደረገ፡ ወደቤተ ሕዝቡ ማስተላለፍ፤ የተፈቀዱትም፡ በሥራ ላይ መዋላቸውን ማረጋገጥ፤

፬ኛ፡ አባልነትን ማጽደቅና ስለአባልነት መልቀቅ፥ መታገድ ወይም መገለል፡ ተነጋግሮ ውሳኔ መስጠት፤

፭ኛ፡ የአገልግሎቱን ቅርንጫፎች መክፈትና ወኪሎችን መሠየም፤

፮ኛ፡ የአማካሪ ሕዋስን፥ እንዲሁም፡ የተለያዩ ጉዳዮችን የሚመለከቱ፥ የሚመረምሩና የሚያጠኑ ተጠሪ ሕዋሳትን፡ ከአባሎች መካከል መርጦ መመደብ፤

፯ኛ፡ እነዚህን የመሳሰሉትን፡ በአገልግሎቱ መመሪያ ውስጥ ተዘርዝረው የተመለከቱትን ዓላማዎች ማከናወን።

ምርፋቁ፡ በኅዳር፥ በየካቲት፥ በግንቦትና በሓምሌ ወሮች ማለቂያ ባሉት፡ በመጨረሻዎቹ ቀዳምያት ሰንበታት (ቅዳሜዎች)፡ መደበኛ ስብሰባውን ያካኼዳል። እንዲሁም፡ ሙሴው፡ አስፈላጊ መስሎ በታየው ጊዜ፡ ምርፋቁ፡ ልዩ ስብሰባ እንዲያደርግ፡ መጥራት ይችላል።

# አንቀጽ አሥራ አንድ

## ስለሕዋሳት

የአገልግሎቱ ተግባርና የሥራ ውጤት፡ ጥራትና ምልዓት ይኖረው ዘንድ፡ ጠቅላላውን ጉባዔና ሙሴውን፥ የሦስቱንም ቤቶች ሊቃነ መናብርት፡ በአሳብና በምክር፥ በጥናትና በምርምር የሚረዱ ሕዋሳት ሊኖሩ ይቻላል። እነዚህንም ሕዋሳት፡ አገልግሎታቸውን የሚፈልገው የአገልግሎት ዘርፍ፡ በየበኩሉ ይመርጣል።

# አንቀጽ አሥራ ኹለት

## አስተዋጽዖ

ለእግዚአብሔር ተብሎ፡ በ“አሥራት፥ በኵራት” ስም ይደረግ የነበረው ክፍያ፡ በዘመነ ፍዳ፡ ሲሠራበት የነበረ፡ የብሉዩ ኪዳን፡ ኦሪታዊ ሥርዓት ሲኾን፡ በዚህ ረገድ፡ በዘመነ ምሕረት፡ በሥራ ላይ የዋለው፡ የአዲሱ ኪዳን መንፈሳዊ ሥርዓት ግን፡ ከዚህ በተለየ፡ ሃይማኖታዊ ብቅዓት የሚፈጸም ኾኗል።

ይኸውም፡ የእግዚአብሔር የቃል ኪዳን ልጆቹ የኾኑት ኢትዮጵያውያን፡ “ኹሉ የእርሱ የኾነው ጌታ፡ ለእኛ የሚለግሠን እንጂ፡ እርሱ፡ ከእኛ የሚወስደው፡ አንዳች ነገር የለም” በማለት፡ የሕይወታቸው ቋሚ መመሪያ ያደረጉትን፡ ቀኖናዊ መርሃቸውን ተከትለው፡ ለፈጣሪያቸው የሚያበረክቱት፡ የገንዘባቸውን “አሥራት”፡ ማለትም፡ “ከአሥር አንድ”፥ ወይም የንብረታቸውን “በኵራት”፡ ማለትም፡ “የመጀመሪያውን ፍሬ” ብቻ አይደለም።

ለፈጣሪያቸው የሚያበረክቱት፡ ራሳቸውንና ሙላውን ገንዘባቸውን፥ እውቀታቸውንና ጉልበታቸውን፥ በጠቅላላ፡ ኹለንተናቸውን፡ ማለትም፡ ነፍሳቸውንና ሥጋቸውን፡ ከነመንፈሳቸው፡ አሥሩንም ክፍል በሙሉ መኾኑን የሚያረጋግጠው ምግባራቸው ነው።

በዚህ መሠረት፡ የአገልግሎቱ አባሎች፡ እያንዳንዳቸው፡ ለየራሳቸውና ለየቤተሰባቸው፡ በግል ለሚያስፈልጋቸው የኑሮ ግዳጅ የሚያደርጉት ወጪና ለሌላው የሚያበረክቱት ምጽዋት፥ ለአምላካቸውም የሚያቀርቡት መባ፡ ኹሉም ተጠቃልሎ፡ ያው፡ የአንዱ እግዚአብሔር ሀብት ስለኾነ፡ “ይህ፡ የእኔ ድርሻ ነው፤ ይህ ደግሞ፡ የእግዚአብሔር ድርሻ ነው” ብለው ለይተውና ለየብቻ መድበው የሚያስቀምጡት ነገር ከቶ የለም።

ስለዚህ፡ የእግዚአብሔር ባለአደራዎች በመኾን፡ ያላቸውን ኹሉ በክብር ይዘው፡ ከየራሳቸው ትዳር ጀምረው፡ እነርሱ ለሚያምኑበት ተገቢ አገልግሎትና በጎ ምግባር እንዲውል ማድረግ፡ የእያንዳንዳቸው ፋንታ፥ ተጠያቂነትና ኃላፊነት መኾኑን ያውቁታል።

እንግዲህ፡ ለአገልግሎቱ የሚያደርጉት አስተዋጽዖ ቢኖር፡ በዚሁ መልክ፡ በፈቃደኛነትና በአቅም ላይ የተመሠረተ ኾኖ፡ በየራሳቸው ይወሰናል። ነገር ግን፡ “የአገልግሎቱን ዓላማ፡ በተቻለ መጠን፡ ከግብ ለማድረስ፡ ለአንዳንድ ተግባሮች ማከናወኛ፡ ገንዘብ ስለሚያስፈልግ፡ አስተዋጽዖውን ወስኖ መመደብ፡ ተገቢ ይኾናል” ብለው፡ አባሎቹ፡ በጠቅላላው ጉባዔ አማካይነት ሲስማሙ፡ አመዳደቡ፡ ይህን የሃይማኖት መመሪያ በመከተል፡ ከዚህ በሚከተለው አሠራር የሚፈጸም ይኾናል።

፩ኛ፡ ቤተ ምልክናው፡ በዚህ ረገድ፡ አጥንቶና አዘጋጅቶ የሚያቀርበውን የገንዘብ ገቢና ወጪ ድልድል፡ ምርፋቁ ተመልክቶ ሲያጸድቀው፡ በሙሴው አማካይነት፡ ለጠቅላላው ጉባዔ ይተላለፋል። ይህም የሒሳብ ድልድል፡ አባሎቹ፡ በየወሩ እና/ወይም በየዓመቱ፥ ከዚያም በላይ፡ ለአገልግሎቱ፡ በፈቃዳቸው የሚያበረክቱት አስተዋጽዖ ቢኖር፡ ያንንና አግባብ ካለው፡ ከሌላም ምንጭ ሊገኝ የሚችለውን ጨምሮ በማመልከት ሊቀርብ ይችላል።

፪ኛ፡ በዚህ መሠረት ተወስኖ፡ አባሎቹ፡ በየወሩ እና/ወይም በየዓመቱ፡ በፈቃዳቸው የሚከፍሉት፡ መደበኛ አስተዋጽዖ ወይም ሌላ ክፍያ ቢኖር፡ ኹሉንም፡ በየመልኩ፡ ማለትም፡ የወሩን፡ በወርኃዊው ስብሰባ ላይ፥ የዓመቱን ደግሞ፡ በእያንዳንዱ የሒሳብ ዓመት፡ ከመስከረም ወር መባቻ ዕለት ጀምረው፡ ባሉት ሰባት ቀኖች፡ ለቤተ ምልክናው መክፈል ይኖርባቸዋል።

፫ኛ፡ ማናቸውም አባል፡ በፈቃዱ ሊሰጥ የገባውን በረከት፡ ወይም መደበኛ አስተዋጽዖ፡ በመጀመሪያ፡ መክፈል ከሚገባው፡ የክፍያ ወራት ወይም ከሂሳቡ ዓመት መግቢያ አንሥቶ፡ በሦስት ወሮች ጊዜ ውስጥ፡ ያለበቂ ምክንያት፡ ሳያበረክት ቢቀር፡ ከቤተ ምልክናው፡ የቃል ወይም የጽሑፍ ማሳሰቢያ እንዲደርሰው ይደረጋል።
ይኸው አባል፡ ማሳሰቢያው ደርሶት፡ በተጨማሪ ለሌላ ሦስት ወሮች፡ ተገቢውን ሳያደርግ ቢቀር፡ በዚህ መምሪያ መሠረት፡ አስፈላጊው የሥነ ምግባር ሥርዓት እንዲፈጸም፡ ጉዳዩ፡ በቤተ ምልክናው ሊቀ መንበር አማካይነት፡ ለምርፋቁ ይቀርባል።

## አንቀጽ አሥራ ሦስት

### የአገልጋዮች አበል

አገልግሎቱን፡ በሥጋዊዉም ኾነ በመንፈሳዊው መስክ፥ በጊዜያዊነትም ኾነ በቋሚነት፥ በኃላፊነትም ኾነ በባልደረብነት፡ ሙሉ ጊዜያቸውን ሰጥተው የሚያገለግሉ ሕዝባውያን፥ ካህናትና ምሉካን ኹሉ፡ ቤተሰብ ካላቸው፡ ለቤተሰባቸው ኑሮ ጭምር፡ የሚያስፈልገው ድርጅት፡ በአገልግሎቱ ይዘጋጃል፤ ወይም የተወሰነው ወጪ፡ ከአገልግሎቱ ይመደብላቸዋል እንጂ፡ ለማናቸውም የአገልግሎቱ ባልደረባ፡ የተወሰነ የወር ደመወዝ የመክፈል አሠራር፡ በአገልግሎቱ ውስጥ ፈጽሞ አይኖርም።

በየራሳቸው የገቢ ምንጭ የሚተዳደሩ ኾነው፡ ነገር ግን፡ በአገልግሎቱ ውስጥ በፈቃዳቸው፡ በነፃ መሣተፍ የሚፈልጉ ቢኖሩ፡ ይህንኑ የአገልግሎት ተሣትፎአታውን ማበርከት ይችላሉ።

## አንቀጽ አሥራ አራት

### ቋንቋና የቀን አቆጣጠር

በቅዱሱ ኪዳን የኢትዮጵያዊነት ሃይማኖት ምክንያት፡ የአገልግሎቱ ቋንቋ፡ ግእዝና ከእርሱ የተገኘው ኢትዮጵያኛ (ዐምሓርኛ) ሲኾን፡ የጊዜ አቆጣጠሩም፡ በእዚሁ ሃይማኖት ላይ የተመሠረተው፡ ኢትዮጵያዊው ሥርዓተ ቀመር ነው።

## አንቀጽ አሥራ አምስት

### ማኅተም

የአገልግሎቱ ማኅተም፡ በቅዱሱ ኪዳን የኢትዮጵያዊነት ሃይማኖት ላይ ተመሥርቶ፥ "ኢትዮጵያ ታበጽሕ እደዊሃ ኀበ እግዚአብሔር" እና "ሞዓ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ" የሚሉትን የእግዚአብሔር ቃላት፡ በሥዕላዊ ምልክት ተርጉሞና የቀስተ ደመና ቀለማት በኾኑት፡ የኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ ተከብቦ የሚታየው ቅርጽ ይኾናል። እርሱም፡ በዚህ መምሪያ ሥርዓት፡ የመጀመሪያ ገጽ ርእስ ላይ ሠፍሮ ባለው መልኩ፡ ገዝፎ ይታያል።

## አንቀጽ አሥራ ስድስት

### የመመሪያው ሥርዓት ምዝገባና መሻሻል

ይህ መመሪያ ሥርዓት፡ በመንፈስ ቅዱስ ተጽፎና ተመዝግቦ የሚገኘው፡ በእያንዳንዱ አባል ልብ ላይና ልቦና ውስጥ ነው።

መመሪያው እንዲሻሻል የሚያስፈልግ የኾነ እንደኾነ፡ ከላይ በአንቀጽ ኹለት እንደተመለከተው፡ ማሻሻያው፡ ከቀኖናዊው መርህ ጋር የሚስማማ መኾኑ፥ እንዲሁም፡ ከአንድ እስከሦስት ያሉት፡ የዚህ መመሪያ አንቀጾችና በእነዚህ ላይ ተመሥርተው የጸደቁት፡ ሌሎቹ፡ የየአንቀጹ ክፍሎች የተጠበቁ መኾናቸው ተረጋግጦ፡ ሊሻሻል ይችላል። ይህም፡ ለምርጫ እንደሚደረገው ኹሉ፡ መላው አባሎች፡ በተለይ ለዚህ ዓላማ፡ ተገቢውን ሱባዔ ፈጽመውና የአገልግሎቱ ጠቅላላ ጉባዔ፡ ከአባሎቹ መካከል፡ እጅግ ቢያንስ፡ ኹለት ሦስተኛዎቹ ተገኝተው፡ የአንድነት ድምፃቸውን በሰጡበት መደበኛ ስብሰባው ላይ ይከናወናል። ማሻሻያውን መርምሮ ውሳኔ የሚሰጠው፡ የአገልግሎቱ ጠቅላላ ጉባዔ ከመካኼዱ፡ ከአሥር ቀኖች በፊት፡ ረቂቁ ሓሳብ በጽሑፍ ተዘጋጅቶ፡ ለእያንዳንዱ አባል ይላካል።

\+ \+ \+

# ከኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት አገልግሎት የተላለፈ፡

## ታላቅና ወሳኝ መልእክት፦

እውነተኛዋን ኢትዮጵያና እውነተኛውን ኢትዮጵያዊነት፡ በራስ ውስጥ፡ መልሶ ለማግኘት ኾነ፥ ወይም፡ በሰዎች መካከል፡ ለማስገኘት የሚያስችለው እውነተኛው ኃይል፡ ያለጥርጥር፡ ከእግዚአብሔር ቃል ኪዳን ብቻ ይመነጫል። እንዲህ በመኾኑም፡ ውጤቱ፡ እንደዘመኑ ሥጋውያን ፈሊጠኞችና መንፈሳውያን ቀንደኞች ሙከራና ጥረት፡ ከንቱ አይደለም።

በዚህ የተፈተነ ኃይል ለመጠቀም ግን፡ እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ፡ ሊከፍለው የሚገባው ጥቂት መሥዋዕትነት አለ፤ ያም፡ በጦር ሜዳ መሰለፍን፥ ሸፍቶ፡ በረሃ መግባትን፥ ወይም፡ ሥጋዊና መንፈሳዊ ድርጅትን አቋቁሞ በየአዳራሹ መሰብሰብን፥ ገንዘብ ማዋጣትን፥ በየጎዳናውና በየአደባባዩም፡ የአቤቱታ ጩኸት ማሰማትን የሚጠይቅ አይደለም።

ከእያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ፡ ከወንዱም፥ ከሴቷም፥ ከሽማግሌውም፥ ከወጣቱም የምትጠበቀው ግዳጅ፡ አንዲት ብቻ ናት፤ እርሷም፡ የእግዚአብሔር የቃል ኪዳን መልእክት የኾነችውን፡ የእውነትና የእውቀት ፍሬ የያዙትን፡ "ኢትዮጵያዊው፡ በማንነቱ ፍለጋ!"፥ "ኢትዮጵያ፡ የዓለሙ መፋረጃ!" እና Ethiopia: The Classic Case የተባሉትን መጻሕፍት፥ በቅርቡም፡ "አንደኛ"፥ "ኹለተኛ" እና "ሦስተኛ" በሚሉ፡ በሦስት ንዑሳን አርእስት፡ በተከታታይ የሚወጣውን፡ "ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት" የሚለውን አዲስ መጽሓፍ ማንበብን የምትጠይቀው ግዳጅ ናት።

እነዚህ፡ ስለኢትዮጵያና ኢትዮጵያውያን፥ ስለኢትዮጵያዊነትና ስለሰባቱ ኪዳናት፡ በዝርዝር የሚያብራሩት መጻሕፍት፡ በዚህ ዕትም ልባስ፡ የውስጥ ገጽ ላይ በተገለጠው፡ በአሳታሚውና በአከፋፋዩ ድርጅት፡ የተለያዩ የአድራሻ መስመሮች፥ እንዲሁም፡ በኢትዮጵያና በተቻለ ዓቅም፡ በመላው ዓለም አገሮች ባሉ፡ የኢትዮጵያውያን የመጻሕፍት ቤቶችና መደብሮች እንዲገኙ ስለተደረገ፡ ጉዳዩ የሚመለከተው ኹሉ፡ ይህን ግዳጁን ይፈጽም ዘንድ፡ አገልግሎቱ ያሳስባል።

# ስለእነዚህ መጻሕፍት አዘጋጅ፡

# አጭር መግለጫ፡፡

ሐምሌ ፫ ቀን፥ ፲፱፻፳፰ ዓ. ም. በአዲስ አበባ መካነ ሰማዕት ቅዱስ ቂርቆስ ቤተ ክርስቲያን ሰበካ የተወለዱት፡ የእነዚህ መጻሕፍት አዘጋጅ፡ ንቡረ እድ ኤርምያስ ከበደ ወልደ-ኢየሱስ፡ ገና በትምህርት ቤት ሣሉ፡ በአሥራ ስምንት ዓመት ዕድሜያቸው፡ “**ምናሴ፥ የመከራዬ ደስታ፡ ዓለምን ረታ!**”፥ በሥራ ዓለምና በደርግ፡ የእሥራትና የግዞት፥ ኋላም የስደት ዘመን ሣሉም፡ ከደረሷቸው መጻሕፍት መካከል፡ “ኢትዮጵያዊው፡ በማንነቱ ፍለጋ!”፥ “ኢትዮጵያ፡ የዓለሙ መፋረጃ!”፥ Ethiopia: The Classic Case እና “ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት” የተባሉትን፡ ለኅትመትና ለንባብ አብቅተዋል፡፡

በ፲፱፻፶፪ ዓ. ም. የመጀመሪያውን፡ የኢትዮጵያ ድርሰት ማኅበር፡ ከጥቂት ደራስያን ጋር አቋቁመው፡ እስከ፲፱፻፷፩ ዓ. ም. ድረስ፡ በዋና ጸሐፊነት፡ የበጎ ፈቃድ አገልግሎታቸውን አበርክተዋል፡፡

በ፲፱፻፶፫ ዓ. ም. በአዲስ አበባ፡ ደቡብ ሕዝብ ተመርጠው፡ የመናገሻ ከተማዋ ማዘጋጃ ቤት ምክር ቤት አባል፥ በ፲፱፻፶፯ ዓ. ም. የቀድሞው፡ የኢትዮጵያ ቤተ ሕዝብ፡ የሕግ መምሪያ ምክር ቤት አባል፥ በ፲፱፻፷፩ ዓ. ም. በንቡረ እድነት ማዕርግ፡ የኢትዮጵያ ቤተ ሕዝብ፥ ቤተ ምልክናና ቤተ ክህነት ሙሉ ተጠሪ በመኾን፡ የአኵስም ጽዮን አስተዳዳሪ፥ በ፲፱፻፷፬ ዓ. ም. የቀድሞው፡ የኢትዮጵያ ቤተ ክህነት ጠቅላይ ሥራ አስኪያጅ፥ በ፲፱፻፷፯ ዓ. ም. በቀድሞው የኢትዮጵያ ቤተ ምልክና፡ የሕግ መወሰኛ ምክር ቤት አባል ኾነው አገልግለዋል፡፡

በዚያ አገልግሎት ላይ እያሉ፡ በሰኔ ፳፬ ቀን፥ ፲፱፻፷፯ ዓ. ም. የሙት በቃ ብያኔ ወደተሰጠበትና ከሰባት ዓመታት በላይ ወደቆዩበት፡ የደርግ እሥር ቤት ገቡ፡፡ በመጨረሻ፡ በእግዚአብሔር ቸርነት፡ ከዚያ ፈተናና መከራ ተርፈው፥ ከእሥርም ተፈትተው፡ ለብዙ ዓመታት፡ በአገራቸው፡ በግዞት፥ በባዕዳን አህጉር ደግሞ፡ በፈቃደኝነት የስደት ኑሮ፡ ተልእኳቸውን በመቀጠል ከቆዩ በኋላ፡ በቅርቡ፡ ወደኢትዮጵያ ለመመለስ በቅተዋል፡፡

ከወይዘሪት ራሔል ዘካርያስ ጋር፡ በሐምሌ ፫ ቀን፥ ፲፱፻፵፰ ዓ. ም.፡ በኢትዮጵያዊው ሥርዓት ከፈጸሙት ጋብቻቸውና የትዳር ኑሮአቸው፡ ሦስት ወንዶችንና አምስት ሴቶች ልጆችን አፍርተዋል፡፡

\+ \+ \+

## **About the Author**

## **of the above-mentoned books and this Publication.**

An Ethiopian, Son, Servant and Messenger of “Ethiopia: The Kingdom of God” with the following biographical sketch:

Name and Title: Ermias Kebede Wolde-Yesus, Nibure-Id (of Aksum Zion). [See pp. 72-78, Ethiopia: The Classic Case, by the same autor, for the explanation of the title.]

Born: on Hamle 3, 1928 ( Ethiopian Calendar; by the Gregorian, July 10, 1936) in Addis Abeba, Ethiopia.

Educated and ordained: by the Grace of God, in Ethiopia.
Married: Rahel Abraham Zekarias in Hamle 22, 1948 (July 29, 1956) and is blessed with three sons and five daughters named: Tnbeete (deceased), Temnaite (deceased in infancy), Melikte, Tmhirte, Sbkete, Haimanote, Semaete and Sbhate.

Served: as Parish Deacon, Priest and Head; as secretary and executive in various departments of the Houses of the Priesthood and the Government of Ethiopia; and as Administrator of Menelik II Foundation.

Elected: by the Covenantal People, from the Addis Abeba Constituency, as member of the City Council and of the Chamber of Deputies in the House of the People (Ethiopian Parliament); and by both the Chamber and the Senate, as President of the Ethiopian Parliament in the Interparliamen- -tary Union whose headquarters is in Geneva, Switzerland.

Appointed: by Atsie Haile Sellassie the First, under the recommendations of the Itchege (Patriarch) of the House of the Priesthood, the Tsehafe-T’izaz (Prime Minister) of the House of the Government and the Liqe-Hizb (President) of the House of the People (Parliament), to the positions of:

1) Nibure-Id of Aksum Zion, constituting the Three Houses of Ethiopia: The Kingdom of God;
2) Megabe Bete K’h’net (Chief Administrator of the House of the Priesthood);
3) Hig Wossagn (Senator) in the House of the People.

Visited: some African, Middle-eastern, Asian, European, North and South American countries, including, officially, England, Germany, Israel, U.S.A., and the former U.S.S.R.

Attended: several local, national, ecumenical and international conferences.

Participated: in numerous social, religious, academic and philanthropic organizations in Ethiopia; and, writing being my secondary vocation, served as founder and the first secretary of the Ethiopian Literary Society.

Detained: in Addis Abeba, Ethiopia, by the revolutionary Communist military junta in 1974 and remained incarcerated until 1981.

Exiled: to the United States of America in 1987 after my release from detention and a period of respite under government surveillance. Ever since: under the banner of "Ethiopia: The Kingdom of God Services", I am preoccupied with the preservation and dissemination of the concepts of the Ethiopian Heritage: by participating in translation works and projects pertaining to Biblical Ethiopia; by conducting prayer services and educational meetings; and, by writing, publishing, lecturing, and traveling.

\+ + +